የኢትዮጵያ
ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ



ሚያዝያ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ

ሚያዝያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. መግቢያ ........................................1
2. የፖሊሲው መነሻዎች........................................2
3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ርዕይ፣ መርሆዎች እና ዓላማዎች........................6
4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮችና አቅጣጫዎች..............................9
4.1 የገጠር መሬት፣ ደን እና ተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም.............9
4.1.1 የገጠር መሬት አስተዳርርና አጠቃቀም ....................9
4.1.2 የደን ሃብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም .................12
4.1.3 የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ አያያዝና አጠቃቀም ................13
4.2 የቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት አቅርቦት ሥርዓት ...............13
4.2.1 የግብርና ምርምርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት.................14
4.2.2 የግብርና ኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት...............14
4.2.3 የእፅዋት ልማትና ጥበቃ ግብዓቶች ....................15
4.2.3.1 የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ግብዓቶች....15
4.2.3.2 የእፅዋት ዘር ሥርዓት ....................16
4.2.3.3 የእፅዋት ጥበቃ ግብዓትና አገልግሎት...............17
4.2.4 የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማትና ጤና ጥበቃ ግብዓቶች .......... 18
4.2.4.1 የእንስሳትና ዓሳ ዝርያ፣ ዘር እና የእርባታ ግብዓት ......... 19
4.2.4.2 የእንስሳትና ዓሳ መኖ ልማት፣ ዝግጅትና አቅርቦት ..........19
4.2.4.3 የእንስሳትና ዓሳ ጤና ጥበቃ ግብዓት እና አገልግሎት.........20
4.2.5 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሥርዓት................ 22
4 .2 .6 የቴክኖሎጂ እና ግብዓት አጠቃቀም የማበረታቻ ሥርዓት.......... 22
4.2.7 የግብዓት ፍላጎት፣ ምርት እና አቅርቦት መከታተያ ሥርዓት..........23
4.3 የግብርና ውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ..........................23
4.4 የምርት ግብይት................................. 24
4.4.1 የግብርና ምርቶች ግብይት ...........................25
4.4.2 የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ አቅርቦትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ ....26
4.4.3 ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት..........27
4.5 የገጠር ልማትና መዋቅራዊ ሽግግርን ማረጋገጥ .................... 27
4.6 የግብርና ልማትን ያማከለ የመሠረተ-ልማት ዝርጋታና አቅርቦት.............28

4.7 ቢዝነስና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት.............................30
4.7.1 የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር.............................31
4.7.2 የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማጠናከር.............................32
4.8 የግብርናና ገጠር ልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነት.............................33
4.9 የዘርፉን የማስፈጸም አቅም መገንባት.............................35
4.9.1 የሰው ኃይል ልማት.............................35
4.9.2 የተቋማት ትብብርና ተጠያቂነት ሥርዓት.............................36
4.9.3 የትምህርት፣ ስልጠና እና የግብርና ዘርፍ ተቋማት ትስስር ሥርዓት.......36
4.9.4 የዲጂታል ግብርና የአሰራር ሥርዓት.............................37
4.9.5 ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት፣ አገልግሎት፣ ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር...38
4.10 የግብርና አካታችነትና ዘላቂነት ማሳደግ.............................39
4.10.1 የአየር ንብረት ለውጥን ያገናዘበ የግብርና ልማት.............39
4.10.2 የምግብ ዋስትና እና አደጋን የመቋቋም አቅም ማጠናከር........39
4.10.3 የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት.............................40
4.10.4 የአካል ጉዳተኞችና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት..40
4.10.5 ዘላቂ የአርብቶ አደር አካባቢ ግብርና ልማት.............................40
4.10.6 የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና ሥርዓት.............................40
**5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች.............................41**
**6. ፖሊሲ የማውጣት ስልጣንና የፖሊሲው ወሰን.............................42**
**7. የፖሊሲው የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች.............................42**
7.1 ፖሊሲውን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት.............................42
7.2 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈጻጸም የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ሥርዓት......44
7.3 ፖሊሲውን ለማስፈጸም የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞች.............................45
7.4 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈጻጸም የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት.......47
**8. ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች.............................50**
8.1 የአምራች ዘርፍና የመሠረተ-ልማት ዘርፍ ፖሊሲዎች.............................50
8.2 ማህበራዊና የሰው ሃብት ልማት ፖሊሲዎች.............................51
8.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ.............................51
**9. መሠረታዊ የቃላት ፍቺ.............................52**

## 1 . መግቢያ

የግብርና ዘርፍ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ውስጥ በ2015 በጀት ዓመት 32.1 በመቶ በላይ ድርሻ የሚሸፍንና የኢኮኖሚ መሠረት በመሆን ለማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚያበረክት የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ነው። የግብርናው ዘርፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በዘላቂነት የማሳደግ እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን እውን የማድረግ ድርብርብ ሚና እንደሚጫወት ይጠበቃል። በመሆኑም በቀጣዮቹ ዓመታት የሚኖረውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሀገሪቱን ሕዝብ የመመገብና ሀገራዊ የምግብ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ፣ በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ የማስገኘት፣ ለኢንዱስትሪውና ለሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች በቂ ግብዓትና የሰው ኃይል የማቅረብ፣ ለሌሎች ዘርፎች ምርቶች ገበያ ወይም ፍላጎት የማጎልበትና በስፋት የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራ ከግብርናው ዘርፍ ይጠበቃል።

የግብርናና ገጠር ልማት የሚመራበት የገጠር ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የማስፈጸሚያ ስልቶች በ1994 ዓ.ም ተቀርጸው ስራ ላይ ውለዋል። ይህንኑ መሠረት ባደረጉና በተከታታይ ዓመታት ሥራ ላይ በዋሉ የልማት ዕቅዶች በሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ ሲጫወት ቆይቷል። ይህን ተከትሎም ዘርፉ ከነበረበት አነስተኛ የእድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ምርትና ምርታማነት እድገት ከማስመዝገቡም ባሻገር የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት እንዲፋጠን የመሪነት ሚናውን ተጫውቷል። በገጠር የነበረው የድህነት ደረጃ ቀንሷል፤ የቤተሰብ ምግብ ዋስትናም ተሻሽሏል።

ሆኖም የዘርፉ እድገት ከአዳጊ የምርት ፍላጎት ጋር አብሮ መጓዝ ባለመቻሉ ምክንያት የምግብ ዋስትና ያልተረጋገጠላቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ይገኛሉ። ለኢንዱስትሪ የሚፈለገውን ጥሬ ዕቃ በበቂ ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ማቅረብ አልተቻለም። በተጨማሪም ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን አቅርቦት ማሳደግና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት አልተቻለም።

ስለሆነም የግብርናና ገጠር ልማት ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ፣ በሀገር ደረጃ እየተከናወኑ ያሉትን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎች እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም እና የግብርናውን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የበለጠ ለማስተሳሰር፣ የተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም፣ የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ እና የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት እና ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክት በሥራ ላይ የነበረው የገጠር ልማት ፖሊሲ በዚህ ፖሊሲ ተተክቷል።

## 2 . የፖሊሲው መነሻዎች

በሥራ ላይ የነበረው የገጠር ልማት ፖሊሲ የግብርናና ገጠር ልማት የሚመራበት አምስት ዋና ዋና እና ተመጋጋቢ የትኩረት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ሲተገበር ነበር። እነዚህም የትኩረት አቅጣጫዎች የሰው ጉልበትን በሰፊው መጠቀም፣ የመሬትና ተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ መጠቀም፣ የተቀናጀና የተለያዩ የግብርና ሥነ-ምህዳሮች ጋር የተጣጣመ፣ በገበያ የሚመራ እና የተቀናጀ የገጠር ልማት ማካሄድ ነበሩ።

ፖሊሲው የቴክኖሎጂና ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም ማስፋፋት፣ በገጠር መሠረተ-ልማት ላይ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰትን ማስፋፋት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የአነስተኛ ይዞታ አርሶና አርብቶ አደር ግብርና ገበያ-መር እንዲሆን ማስቻል፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማጠናከር እንዲሁም ግብርና ነክ ያልሆኑ የገጠር ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት ላይ ያተኮረ ሲሆን በዋናነት በመንግሥት የተመራና የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ ነው። መንግስት ይህን ፖሊሲ ነድፎ በተገበረባቸው ዓመታት የግብርናው ዘርፍ እያደገና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት እንዲፋጠን በማድረግ ለተደረሰበት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት የመሪነት ሚናውን ተጫውቷል።

ፖሊሲው በተሟላ የህግ ማዕቀፍ አለመደገፉ እና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ግልፅ አቅጣጫ አለማስቀመጡ፣ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን (መሬት፣ ጉልበትና ካፒታል) አቀናጅቶ ምርታማነት ማሳደግ ላይ በቂ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ትርጉም ያለው የማበረታቻ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤ የመንግስትን ሚና ያጎላ እና የሌሎች የባለድርሻ አካላትን ሚና በግልፅ አለማስቀመጡና ለተሳትፏቸው ውጤታማነት የሚያግዝ የማበረታቻ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ ለእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት እንዲሁም ለዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ተገቢ ትኩረት አለመሰጠቱ፣ ዘርፉን የሚመጥን ፋይናንስ (ብድር፣ ኢንሹራንስ እና አማራጭ ፋይናንስ) አለመቅረቡ፣ የተሟላ የማስፈፀሚያ ማዕቀፍ አለመዘርጋቱ እና የማስፈፀም አቅም ለመገንባት አለመቻሉ የታሰበውን ያህል ውጤት ማምጣት አላስቻለም።

በዚህም የተነሳ ዘርፉ በአብዛኛው አነስተኛ ይዞታ ባለውና ለፍጆታ በሚያመርት፣ ዝቅተኛ ቴክኖሎጂ በሚጠቀም፣ በዝናብ ላይ ጥገኛ በሆነ አርሶና አርብቶ አደር የሚከናወን መሆኑና የደንና ተፈጥሮ ሃብት መመናመንና መጎሳቆልን ያስከተለ ሆኖ እንዲቀጥል አስገድዶታል። ይህም የግብርና ምርታማነት እድገት በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት እንዳይራመድ አድርጎታል። በተመሳሳይ ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው የግብርና ምርቶች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ምርቶች የመሸጋገር ሂደቱ ዘገምተኛ ሆኗል። በተጨማሪም የሚመረተው ምርት የራስ ፍጆታን አሟልቶ ለገበያ ሊቀርብ የሚችለው መጠን አነስተኛ በመሆኑ ግብርና በተሟላ መልኩ ገበያ-መር እንዳይሆን ብሎም የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ (የግብርና ትራንስፎርሜሽን)

አዝጋሚ እንዲሆን አድርጎታል። የዘርፉ የሰው ኃይል ምርታማነት እድገት በሚፈለገው ፍጥነት ባለመጓዙ ካለው አጠቃላይ አምራች የሰው ኃይል በዘርፉ የተሰማራውን ድርሻ በመቀነስ ወደ ሌሎች ዘርፎች በተለይም ወደ ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚው የተሸጋገረው የሰው ኃይል አነስተኛ ነው። ከመስኖ አለመስፋፋትና የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት አለመዳበር ጋር ተዳምሮ ዘርፉ አሁንም ከዝናብ ጥገኝነት ባለመላቀቁ በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅ በግብርና የተሰማራውን የህብረተሰብ ክፍል ክፉኛ ከመጉዳቱ ባሻገር የሀገርን ኢኮኖሚ እየፈተነው ይገኛል። በሌላ በኩል የግሉ ዘርፍ በተፈላጊ የግብርና ግብዓቶች አቅርቦትና በሰፋፊ የግብርና ልማት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፍ መሳብና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ አልተቻለም።

የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም የአፈርን ልዩ ባህሪያት ከግምት ውስጥ ያላስገባና በሂደት እየቀነሰ የመጣውን የአፈር ለምነትና ጤንነት ችግር ለመፍታት የሚያስችል መደላድል ሳይፈጥር ቆይቷል። በተለይም በአሲዳማነት የተጠቃ መሬት ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ውጤታማነት በእጅጉ እንዲቀንስ አድርጎታል። በተጨማሪም የጥምር እርሻ ደን ዘዴ ከምግብ ዋስትናና ገቢ ማስገኛ ቀጥተኛ ጥቅሞች ባለፈ የአካባቢ ተፈጥሯዊ ሚዛንን የጠበቀ ግብርና ልማት ለማጎልበት በሚያስችል የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍና ተቋማዊ አደረጃጀት አልተመራም።

የመሠረተ-ልማት ዝርጋታዎች የልማት አካባቢዎችን በግብርና የመልማት አቅምን በበቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያላስገቡ፣ የተገነቡትም በበቂ መጠንና በሚፈለገው ጥራት ባለመስፋፋታቸው የግብርና ልማቱን ገድበውታል። እነዚህ ውስን የመሠረተ-ልማት ዝርጋታዎች በመንግስት በጀት ላይ የተንጠለጠሉ ከመሆኑ ባሻገር አስተዳደራቸውም ወጥና ጠንካራ ባለቤት እንዲኖረው አልተደገረም። በዚህም ምክንያት የግብርና ምርቶች ጥራታቸው ተጠብቆ ወደ መዳረሻ ገበያ እንዲደርሱ የሚያስችሉ የማቀዝቀዣ ሰንሰለት የተሟላላቸው የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አቅርቦት እጥረት በተለይም ዘመናዊ የእንስሳት ማጓጓዣ መኪኖች በበቂ አልቀረቡም። በመሆኑም ለሀገር ውስጥና ለወጪ ንግድ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት በዕቃ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እንዲጓጓዙ መደረጉ እና ለመሠረተ-ልማት ግንባታ በቂ የብድር አገልግሎት አለመመቻቸቱ ዘርፉ እንዳይዘምን ገድቦት ቆይቷል። ከዚህም በተጨማሪ የግብርና ምርትና ግብዓት ማከማቻ/ማቆያና ማቀነባበሪያ፣ የግብይት ማዕከላት፣ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቱ የተሟላ መጋዘንኖች በበቂ ደረጃ አለመኖር እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት አለመዘርጋት የምርት ብክነትና ጥራት ጉድለት እንዲሁም በአምራቾች፣ በተጠቃሚው እና በሀገራዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል።

የግብርና ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት አሳክቶ ከዘርፉ የሚመነጨውን ሃብት ለገጠር ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ፈጥሮ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ማስተሳሰርን፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ማስፋፋትን፣ የገጠርና ከተሞች ትስስርን ጨምሮ እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችንና

አገልግሎቶችን ማስፋፋትን የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ አልተቀመጠም። ይህንንም የሚያስተባብርና የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀትም በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም።

የግብርና ልማትን ከዘላቂ ተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ጋር ጎን ለጎን ለማከናወን የህግ ማዕቀፎች ባለመነደፋቸው እንዲሁም ተቋማዊ ቅንጅት የሚፈጥር የአሰራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ፖሊሲውን በውጤታማነት ለመተግበር አዳጋች አድርጎታል።በዚህም የአየር ንብረት ለውጥ በሰብልና እንስሳት ልማት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ በመፍጠር ግብርናውን ይበልጥ ለተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ አድርጎታል። ከዚህ በተጨማሪ አርሶና አርብቶ አደሩ መሬቱን በአግባቡ በመንከባከብ ጥቅም ላይ እንዲያውል አስገዳጅ ሁኔታ ባለመኖሩ የወል ይዞታ ያላቸውን የግጦሽ መሬት፣ የደን ቦታ፣ የከርሰ-ምድር ውሃን የሚሞሉ ውሃ አዘል መሬቶች የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስባቸው አስገድዷል። ይህም ሀገሪቷ ወደፊት የሚገጥማትን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚኖራትን የተሻለ ዕድል ይበልጥ እንዲጠብ አድርጎታል።

በሀገራችን የመልካዓ ምድራዊ አቀማመጥ ዝቅተኛ የሆኑ አካባቢዎች ከጠቅላላው የቆዳ ስፋት ከ60 በመቶ በላይ የሚሸፍን ሲሆን ከ15 በመቶ በላይ ህዝብ ይኖርበታል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚካሄዱ የግብርናና ገጠር ልማት ስራዎች የአካባቢውን ሥርዓተ-ምህዳርና የዝናብ ሁኔታ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የእንስሳት ሃብት የመልማት አቅም፣ የኑሮ ዘይቤ ባገናዘበ መልኩ የተቀናጀና ዘላቂ ልማት ስራዎችን ለመቃኘት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት አልዳበረም። ይህንን የሚመራና የሚያስተባብር ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር አልተዘረጋም።

የልማት ስራዎች አካባቢውንና የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ከግምት ውስጥ ያላስገቡና የትኩረት ማነስና ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ውጤታማ በሆነው የባህላዊና ልማዳዊ ዕውቀት ላይ ተመስርቶ ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ ከሚከናወነው የእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን በተፋሰስ አካባቢዎች በማስፈር በሂደትም ወደ አርሶ አደርነት የመቀየር፣ የስራ እና የአኗኗር ባህሉንም የመለወጥ ስልት እንዲቀመጥ አልተደረገም። የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓቱም በአብዛኛው ሰብል ተኮር የምርት ሥርዓቶች ላይ ትኩረት የሰጠ በመሆኑ በአካባቢው ሲተገበሩ የነበሩት የግብርና እና የኑሮ ማሻሻያ ሥራዎች በተለይም በእንስሳት ሃብት ልማት ላይ የተፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም። በተመሳሳይም የምርምር፣ የቴክኖሎጂና ግብዓት፣ የፋይናንስ አቅርቦትና ሥርጭት ሥርዓቱም የተጠናከረ አልነበረም።

በእነዚህ አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደሩም የአካባቢውን ባህላዊ የመሬት ስሪት ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ሰፊ የሆነው የግጦሽ መሬት

ከህብረተሰቡ አኗኗር ውጪ ለሆነ አገልግሎት እንዲውል መደረጉና በዚህም ተፈላጊ የሆኑ የግጦሽና የውኃ መጠቀሚያ ኮሪደሮች መዘጋት፣ ተደጋጋሚ ድርቅና የአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢው ሥርዓተ-ምህዳር ላይ ጉዳት በማስከተሉ በህብረተሰቡ አኗኗር ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩ፣ ሰፋፊ የግጦሽና በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት በመጤ እፅዋትና ቁጥቋጦዎች መወረር እና የማህበረሰቡ ባህላዊ እውቀት ትኩረት መነፈግና ተቋማቱ እየተዳከሙና ብሎም እየጠፉ መሄዳቸው ለተለያዩ ችግሮች ዳርገውታል። እንዲሁም አካባቢው በአብዛኛው ወቅቱን ያልጠበቀና አነስተኛ የዝናብ መጠን የሚያገኝ ከመሆኑም በላይ በሚከሰተው ከፍተኛ የአየር ሙቀትና የአፈር ክለት የተነሳ፤ ከሚዘንበው ዝናብ አብላጫው በትነትና በጎርፍ አማካኝነት የሚባክን በመሆኑ ለተደጋጋሚ ድርቅ ተጋላጭ ነው። ባለፉት ዓመታት በሀገራችን የግብርና እድገት ቢመዘገብም ይህ ነው የሚባል የቴክኖሎጂና አገልግሎት አጠቃቀም ለውጥ ባለማስከተሉ እንዲሁም በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ባለመስፋፋታቸው ቁጥሩ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የተማረ የገጠር ወጣት ሳቢና ቀጣሪ መሆን አልቻለም።

የገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ በተፈለገው ደረጃና ስፋት ለመተግበር የመረጃ፣ የእውቀትና የአመለካከት ችግሮች፣ የግብርና ሙያ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ፣ የግብርና ባለሙያዎች ተደራጅተው በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ በሙያው ለመሰማራት ያለው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ ለወጣቶች የሚደረገዉ ድጋፍ ዉስን መሆን፣ የመሬት አቅርቦት፣ የፋይናንስ አቅርቦትና አፈጻፀም ችግሮች፣ የስልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት አለመስፋፋት፣ የገበያ አቅርቦትና ትስስር ማነስ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት፣ የመሠረተ-ልማት በበቂ አለመስፋፋት፣ በየደረጃው ያሉ ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት የአቅም ውስንነት እንዲሁም በግብርና የስራ ዘርፍ ለመስራት የወጣቶች የአመለካከት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከመደበኛው እንቅስቃሴ የተለየና ዘርፈ-ብዙ የሆነ አዲስ አስተሳሰብና አቅጣጫ የሚጠቁሙ ሀሳቦችን ማጎልበት እና ስራ አጥነት የሀገሪቱ ቁልፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግር ከመሆኑ አንፃር የግብርናው ስራ ዘርፈ-ብዙ የሆነ አዲስ አስተሳሰብና አቅጣጫ የሚጠቁም እና የዜጎችን የሥራ ዕድል ጥያቄ በአግባቡ መመለስ የሚችል መሆን ይኖርበታል። የመሬት አቅርቦትና ተጠቃሚነትን ማሻሻል፣ ለግብርና መዘመን የሚያስፈለገውን ቴክኖሎጂና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ለማስቻል፣ በዘመናዊ ግብርና አሳታፊ እና በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ተሳትፎ ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

በመሆኑም፣ በአጠቃላይ ሲታይ ዘርፉ ሀገራዊ የምግብ ፍጆታ ማሟላት ባለማስቻሉ የማይናቅ ቁጥር ያለው የሀገሪቱ ህዝብ በቂና የተመጣጠነ ምግብ የማያገኝበትና ሌሎች ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በዕለት ደራሽ እርዳታና በልማታዊ ሴፍቲኔት ጥገኛ ሆነዋል። በተጨማሪም ከዘርፉ የሚገኘው የምርት እድገት

እና የግብይት ሥርዓት ውስን በመሆኑ ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን ማሳደግና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት የሚውል በቂ ምርት ማቅረብ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ለመተካት አልተቻለም።

በሌላ በኩል ሲታይ ሀገራችን ካላት የሥርዓተ-ምህዳር አወቃቀርና አቀማመጥ ተለያይነት የተነሳ የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ የሚያስችል ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት እና የአየር ንብረት እምቅ አቅም፣ ሰፊ የገበያ እድሎች እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገትን ተከትሎ የሚመጣው የግብርና ምርት መጠንና ዓይነት ፍጆታ መጨመር ምክንያቶች ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ የሚያስችሉ ያልተጠቀምናቸው መልካም አጋጣሚዎች አሉን።

## 3 . የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ርዕይ፣ መርሆዎች እና ዓላማዎች

### የፖሊሲው መከለስ አስፈላጊነት

በሥራ ላይ የነበረውን የገጠር ልማት ፖሊሲ በሚከተሉት ምክንያቶች መከለስ አስፈላጊ ሆኗል፦

- ቀደም ሲል ሀገሪቱ ትከተለው የነበረው የግብርና መር የልማት ፖሊሲ ወደ ብዝሃ-ዘርፍ የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ በመቀየሩ ከዚሁ ጋር የተስማማ ፖሊሲ ስላስፈለገ፤
- ገበያን መሠረት ያደረገ የግብርና ምርት አቅርቦትን በማስፋት እና ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እንዲሁም በሂደት የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚውን ወደሚመራበት ደረጃ ማድረስ የተቀመጡትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ከግብርናና ገጠር ልማት ዘርፍ አጣጥሞ ለመምራት፣
- ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባህሪያት ጋር የሚመጡ ለውጦችን ለማስተናገድ እንዲሁም የዘርፉን መልካም አጋጣሚዎችና የመልማት አቅም በስፋት በመጠቀም የዘርፉን ምርትና ምርታማነት እድገት ለማረጋገጥ፣
- የመሬት፣ ደንና የተፈጥሮ ሃብትን በዘላቂነት በመጠቀም የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማረጋገጥ ዘርፉ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ብሎም የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና መረጋገጥ ጉልህ ሚና እንዲጫወት ለማስቻል፣
- የመሬት ስሪት እና ሥርዓት የግብርናን ምርታማነት እና ዘላቂነት ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ እንደ ሀገር ተፈትሾ ለማሻሻል፣ የገጠር መሬት አስተዳደርንና አጠቃቀምን እንዲያሻሽል፣ የተበጣጠሱ የእርሻ መሬት ይዞታዎችን በፈቃደኝነት ኩታገጠም በማድረግና ማዋሃድ እንዲያስችል

እንዲሁም የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማዊ አደረጃጀት ዘላቂና የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም በሚያሰፍን መልኩ ለመምራት በማስፈለጉ፣

- ➔ ግብርናን በቴክሎጂና በሳይንስ የተመራ እንዲሆን ለማድረግ በመንግስት የምርምርና ስርፀት ላይ ተወስኖ የነበረውን አሰራር በውጤታማ የግል ዘርፍ እንዲታገዝ ለማድረግ እና የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት እንዲጠናከር እንዲሁም የግልና የመንግስትን ሚና በአግባቡ መለየት እና ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣
- ➔ የግብርና ኮሜርሻላይዜሽንን በማሻሻል የወጪ ንግድ ምርቶችን ለማሳደግ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ እና የሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ ትርጉም ያለው ማበረታቻ በመስጠት ለፍጆታ ከማምረት ባለፈ ለገበያ የሚያመርቱ እንዲሆኑ ማስቻል፣ ብሎም አርሶና አርብቶ አደሩን ወደ ባለሃብትነት ለማሸጋገር አስፈላጊ በመሆኑ፣
- ➔ የተሟላና ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት ያልተዘረጋላቸው የፖሊሲ ጉዳዮችን በዚህ ፖሊሲ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ለመንደፍ እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣
- ➔ የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር ጥምር ግብርና፣ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ፣ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች፣ ከተማና ከተማ ዙሪያ ግብርና፣ የመካከለኛና ሰፋፊ ግብርና እና የተፈጥሮ ደን አካባቢ ባካተተ መልኩ በትኩረት መምራት በማስፈለጉ፣
- ➔ የግብርናን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ለማስተሳሰርና የገጠር መዋቅራዊ ሽግግሩን ለማሳካት የግብርናና ገጠር ልማት ፋይናንስ አቅርቦት ለማሻሻል፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣ የከተማና ገጠር ትስስርን የሚያጠናክር እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ - ልማቶችንና አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማስተባበር አስፈላጊ በመሆኑ፤
- ➔ የግብርና ልማት ዘላቂ እና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮችን፣ የሴቶችን፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞችን ፍትሃዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ እና የተፈጥሮ መዛባት የማይበገር የግብርና ልማት እውን ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ ይህ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ተዘጋጅቷል።

**ርዕይ**

በ2030 ዓ.ም ግብርናን በማሻገር በገጠር መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ለሀገር ብልፅግና ጉልህ ሚና ተጫውቶ ማየት።

## የፖሊሲው መርሆዎች

ሀገሪቷ የምትከተለውን የብዝሃ-ዘርፍ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ለማሳካት የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲው በሚከተሉት መርሆዎች መሠረት የሚመራ ይሆናል።

- የግል ዘርፉ፣ የህብረት ስራ ማህበራት እና የሌሎች ተዋንያኖች ተሳትፎ ይበልጥ እንዲጠናከርና እንዲሰፋ አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠርና ፍትሃዊ የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖር ለማድረግ መንግስት ፖሊሲና የማስፈጸሚያ ሥልቶች በመቅረጽ እንዲሁም አስተዳደራዊ የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል፣
- መንግስት በገበያ ውስጥ ጉድለትን ለመሙላት ወጪ ቆጣቢነት እና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ ጣልቃ የሚገባ ሲሆን ከገበያ ሥርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፣
- የምግብ ማምረትና አቅርቦት ሂደት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በንጥረ-ነገር ይዘቱ የበለፀገ፣ ትኩስ (ፍሬሽ) እና ተመጣጣኝ ዋጋን መሠረት ያደረገ እንዲሆን በመርህ ደረጃ ተይዞ የሚሰራ ሲሆን ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ፣ ጤናማ አካባቢ እና ጠንካራና ጤነኛ የገጠር ህብረተሰብ መፍጠርን ማዕከል ያደረጉ ተግባራት ይከናወናሉ፣
- የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገትንና ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ከዝናብ ጥገኝነት የተላቀቀ የግብርና ልማት ዘይቤ የሚከተል፣ የአካባቢ፣ የተፈጥሮና ብዝሃ-ሕይወት ሃብት እንክብካቤና አጠቃቀም ውጤታማነትን ለመጨመር እና የአካባቢ ሚዛንን ለማስጠበቅ በየጊዜው የሚከሰቱ የአየር ንብረት ለውጥ እና የተፈጥሮ መዛባት ያገናዘበ የግብርና ልማት እንዲተገበር ይደረጋል፣
- የግብርናና ገጠር ልማት የአካባቢዎችን የመልማት አቅም እና የገጠርና የከተማ ትስስር ማጠናከርን መሠረት ማድረግ፣
- ሀገራችን የተቀበለቻቸውን ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን እና ግቦችን በተጣጣመ ሁኔታ ማስፈፀምና፣
- የፖሊሲውን አፈፃጸም ውጤታማ ለማድረግ ቅንጅታዊ አሰራር፣ ፈጠራን መሰረት ያደረገ እና በዘመናዊ መረጃ ሥርዓት እንዲደገፍ ማድረግ የምንከተላቸው ዋና ዋና መርሆዎች ናቸው።

## የፖሊሲው ዓላማዎች

የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፦

- ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ማረጋገጥ፣

- ለሀገራዊ የምግብና ሥነ ምግብ ዋስትና እና የምግብ ሉዓላዊነት እንዲረጋገጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ማድረግ፣
- ግብርናን ኮሜርሻላይዝ በማድረግ እና በማዘመን ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ማቅረብ፣
- የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃን በማሻሻል ዘላቂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣
- የደን ልማትና አጠቃቀም በማሳደግ ሀገራዊ የደን ውጤት ፍላጎትን ማሟላት ፣
- የስነ-ምህዳር ደህንነቱ የተጠበቀና ኢኮኖሚያዊ አዋጭ የሆነ የግብርና ልማት ዘይቤ በመከተል በአየር ንብረትና በሌሎች የተፈጥሮ ክስተቶች ተፅዕኖ የሚመጣ ተጋላጭነትን መቋቋም የሚያስችል አቅም ማሳደግ፣
- በገጠር የኢኮኖሚና የማህበራዊ መሠረተ-ልማቶችን በማስፋት እና የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር በማረጋገጥ፣ ብሎም የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ የአኗኗር ዘይቤ በመቀየር ህይወቱን ማሻሻል ናቸው።

## 4 . የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮችና አቅጣጫዎች

ግብርናን በማሻገር በገጠር መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ለሀገር ብልፅግና ጉልህ ሚና ተጫውቶ ማየት የሚለውን የዘርፉን ርዕይ እና የዘርፉን ስትራቴጂክ ግብና ዓላማ ለማሳካት እንዲያስችል ዘጠኝ ዋና ዋና የትኩረት መስኮች እንዲሁም የግብርና አካታችነትና ዘላቂነት ጉዳዮች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። እነዚህም የገጠር መሬት፣ ደንና ተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ የቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት አቅርቦት ሥርዓት፣ የውሃ አጠቃቀም እና አስተዳደር፣ የምርት ግብይት፣ የገጠር ኢኮኖሚ ልማት፣ መሠረተ-ልማት፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሳደግና ማጠናከር፣ የግብርናና ገጠር ልማት ፋይናንስ ሥርዓት፣ ተቋማዊ የአሰራር ሥርዓት እንዲሁም የግብርና አካታችነትና ዘላቂነት ጉዳዮች ናቸው።

### 4.1 የገጠር መሬት፣ ደን እና ተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም

መሬት፣ ደንና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ መጠበቅ፣ መጠቀምና ማስተዳደር ብሎም ከሰው ኃይልና ካፒታል ጋር ማጣመር ለዘላቂ የግብርና እድገት መሳካት ወሳኝ ነው። ስለሆነም ይህንን ዓላማ ለማሳካት የመሬት፣ ደን እና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳይ እና አቅጣጫዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 4.1.1 የገጠር መሬት አስተዳርርና አጠቃቀም

የመሬት አጠቃቀምን በተቀናጀ መልኩ አቅዶ መጠቀም መሬት ለልማት የላቀ አስተዋጽዖ ማበርከት በሚችልበት ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል። ይህም ግብርና በመሬቱ የመልማት አቅም እየተለየ እንዲለማ በማስቻል ዘላቂ የግብርና

ልማት ለማከናወን ይረዳል። ነባሩ ፖሊሲ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ዕቅድ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑንና ይህም ስነ-ምህዳርን መሠረት አድርጎ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጧል። ሆኖም በጥቅል የተቀመጠውን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አስገዳጅ የሆነ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ዕቅድ አልወጣም። በመሆኑም የተለያዩ ዘርፎች ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ የልማት እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም ተግባራት ጋር ማቀናጀት አልተቻለም። በሌላ በኩል በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው መሬት በጎሣ ወይም በባህላዊ አሰራር ላይ የተመሠረተ የወል የመሬት ይዞታ ስሪት ስለሆነ ለዚህ ስሪት እውቅና መስጠትና አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል።

የገጠር መሬትን በአግባቡ ማስተዳደርና መጠቀም የአርሶና አርብቶ አደር የይዞታ ዋስትና ለማስከበርና ለማጠናከር የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀም በማሳደግ እንዲሁም የመሬት አጠቃቀምን በማበረታታት ዘላቂ የግብርና እድገት እውን ለማድረግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የመሬት ይዞታ ዋስትናን ለማስከበር የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ሥርዓት በመዘርጋት ሰፊ ስራ በመሰራቱ የይዞታ ዋስትናን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በሌላ በኩል በስራ ላይ ያለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የምዝገባና ቅየሳ ስራዎችን ሊያግዙ የሚችሉ ዝርዝር ድንጋጌዎች አለመያዙ፣ ባለይዞታው በግሉ በመሬቱ ላይ ያለማውን መሸጥ አለማስቻሉ፣ በይዞታ የመጠቀም መብትን ለብድር ማስያዣነት አለመፍቀድ፣ የይዞታ መብትን ለፈለጉት ሰው በስጦታ፣ በውርስና በኪራይ እና በሊዝ ማስተላለፍ አለማስቻሉ፣ ባህላዊ የመሬት አስተዳደርን ግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ፣ የመሬት ኪራይና ማስጠመድ የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ዋና ዋናዎቹ ክፍተቶቹ ናቸው። በተጨማሪም የአርሶና አርብቶ አደር የመሬት ይዞታዎች ወደ ከተማ ክልል ሲካተቱ የይዞታዎች ዋስትና ለማስቀጠል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት ባለመኖሩ ትክክለኛ ባልሆነ ካሳ ባለይዞታዎቹን ማፈናቀል በስፋት ይስተዋላል።

በሀገራችን ግብርና አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች የሚካሄድ ሲሆን የእርሻ መሬቶቹም በአብዛኛው አነስተኛ ስፋት ያላቸው፣ የተበጣጠሱና የተበታተኑ ናቸው። እነዚህን ይዞታዎች በማሰባሰብና በማዋሃድ መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች እንዲፈጠሩ በማገዝ የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀማቸውን በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን መጨመር፣ የምርት ጥራትን ማሻሻል እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ መጠቀም እንደሚቻል ታይቷል። በተጨማሪም የተሰባሰበ ይዞታ ከባለሃብት ጋር የወል እርሻ ልማትን ሳቢና አዋጪ ያደርጋል እንዲሁም የቴክኖሎጂና የግብዓት ፍላጎት ማደግን ተከትሎ ለተደራጁ ወጣቶች አገልግሎቱን በማቅረብ ሰፊ የስራ ዕድል ይፈጥራል። በመሆኑም እነዚህን የፖሊሲ ክፍተቶች እና በዘርፉ ላይ የተፈጠረውን ተግዳሮት ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

- ➔ የመሬት አጠቃቀም በጥናትና በዕቅድ ላይ በመመስረት የገጠር መሬት እንደ መልማት አቅሙ ለተገቢው አገልግሎት ለማዋል፣ የገጠርና የከተማ የመሬት አጠቃቀምን ተመጋጋቢ ለማድረግ፣ ዘላቂ ያልሆነ የመሬት አጠቃቀምን ለማስወገድ፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በመሬት አጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠሩ የመሬት ሽሚያ እና ግጭት ለመቀነስ የተቀናጀ መሬት አጠቃቀም እንዲሰፍን ይደረጋል፣
- ➔ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን በተሻለ ሁኔታ ለመምራት ተበታትነው የሚገኙ የመሬት አስተዳደር አደረጃጀቶችን ወደ አንድ በማምጣት ገለልተኛ እና ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲኖር ይደረጋል፤ ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ በአርሻ መሬት ላይ የሚደረግ ወረራ የሚከላከል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የገጠር መሬት ይዞታን የመጠቀም መብትን ለብድር ማስያዧነት ማዋል፣ የይዞታ መብትን አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት በስጦታ፣ በውርስና በኪራይ ማስተላለፍ እና ባለይዞታው በግሉ በመሬቱ ላይ ያለማውን ሃብት ወይም ንብረት መሸጥ ይፈቀዳል፣ የመሬት ሊዝ፣ ኪራይና ማስጠመድ የተቀላጠፈ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ➔ የመሬት ይዞታ የካሳ አከፋፈል የይዞታውን የመልማት አቅም እና በመሬቱ ላይ የለማውን ሃብት ወይም ንብረት ከግምት የሚያስገባ፣ በይዞታው ከአልሚው ድርሻ እንዲያገኝ እና ሌሎች አማራጭ የካሳ ዓይነቶችን መሠረት ያደረገ እና በተመሰከረለት ገማች አማካኝነት እንዲፈፀም ይደረጋል፣
- ➔ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የህግ ማዕቀፍ የአርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደር የወል መሬት አስተዳደር እና ከአንድ በላይ ጋብቻ የሚመነጩ የመሬት ነክ ጉዳዮችን እንዲያስተናግድ ይደረጋል፣
- ➔ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የይዞታ ምዝገባና ቅየሳ ስራዎችን ወጥ ለማድረግ የምዝገባና ቅየሳ መሳሪያዎች ዓይነት እና ስልቶች በግልፅ ይደነገጋል፣
- ➔ በከተማ ዳርቻ የአርሶና አርብቶ አደር ይዞታ ወደ ከተማ ሲካለል የመሬት ይዞታ መብት እንዲጠበቅ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የተበጣጠሱና የተበታተኑ የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች በፈቃዳቸው በጋራ ባለቤትነት፣ በመከራየት ወይም በመለዋወጥ ማሳዎቻቸውን አሰባስበው እንዲያርሱ፣ ምርት እንዲያሰባስቡ፣ እሴት እንዲጨምሩና እንዲገበያዩ በሂደት እውቀትና ሃብት ካላቸው ጋር አዋህደው መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች እንዲፈጠሩ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.1.2 የደን ሃብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም

የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በተገቢው መንገድ በማከናወን የተለያዩ የደን ውጤቶችን ለሀገር ውስጥ ገበያና ለወጪ ንግድ በማቅረብ የውጪ ምንዛሬ ገቢ ምንጭና የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትንና የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ እያደገ የመጣውን የማገዶና የግንባታ ፍላጎትን ለማሟላት ያስችላል። የጥምር ደን እርሻ ልማት የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢና የኑሮ ደረጃ በዘላቂነት ለማሻሻል ያስችላል። እንዲሁም ሌሎች ኢኮ-ሲስተም አገልግሎቶችን በማሻሻል የአፈር መሸርሸርን በመቀነስ የኃይል ማመንጫና የመስኖ ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ በማድረግ ለኃይል አቅርቦት እና ለግብርና ምርት እድገት አስተዋጽዖ በማድረግ የአረንጓዴ ኢኮኖሚውን ግንባታ ያሳካል። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ካላት የደን እምቅ አቅምና የደን ውጤቶች ፍላጎት አንጻር ለደን ልማትና ለደን ውጤቶች በሚፈለገው ደረጃ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

- ➔ የደን ልማት በተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፤ የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ደኖችን ለማልማት፣ ለመንከባከብ፤ ለመከለል፤ ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የደን እሳትን አስቀድሞ ለመተንበይ፣ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ሥርዓትና መሠረተ-ልማት ይዘረጋል፣
- ➔ የግልና ማህበረሰብ ደንና የደን መሬት የመጠቀም መብት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፣
- ➔ አነስተኛና ሰፋፊ ምርት ሰጪ ደን ለማልማትና እሴት ለመጨመር እና ከውጪ የሚገቡ የደን ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚያስፈልጉ የመሬት፣ የቴክኖሎጂና የፋይናንስ አቅርቦትና ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፣
- ➔ በግል ባለሃብቱ፣ በመንግስት እና በግልና በመንግስት አጋርነት ደን እንዲለማ፣ እንዲጠበቅ እና ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፣
- ➔ የደን ልማትና አጠባበቅ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን በማሳደግ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማረጋገጥ እና ሀገራችን የተቀበለቻቸውን ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችና ግቦች እንዲሳኩ በትኩረት ይሰራል።

### 4.1.3 የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ አያያዝና አጠቃቀም

የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ጤናማ አካባቢን በመፍጠር፣ ዘላቂ የግብርና ልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል። ይሁን እንጂ በሀገራችን የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም የአፈርን ልዩ ባህሪያት ከግምት ውስጥ ያላስገባና በሂደት እየቀነሰ የመጣውን የአፈር ለምነትና ጤንነት ለመፍታት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ሳይፈጥር ቆይቷል። በተለይም በአሲዳማነት የተጠቃ መሬት ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ውጤታማነት በእጅጉ እንዲቀንስ አድርጎታል። በተጨማሪም የጥምር እርሻ ደን ዘዴ ለምግብ ዋስትናና ገቢ ማስገኛ ቀጥተኛ ጥቅሞች ባለፈ የአካባቢ ተፈጥሯዊ ሚዛንን የጠበቀ ግብርና ልማት ለማጎልበት በሚያስችል ደረጃ አልተመራም። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

- ➔ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድን መሠረት ያደረገ፣ ተፋሰስን ያማከለ፣ የውሃ፣ የእፅዋትና የአፈር ባህሪያትን ታሳቢ እንዲያደርግ ይደረጋል፣
- ➔ የጥምር እርሻ ደን ዘዴ እንዲስፋፋ ይደረጋል፤
- ➔ የአፈር ለምነትና ጤንነት ጥበቃ የተፈጥሮ ቁስ፣ አካልና ንጥረ-ነገር ይዘት፣ አሲዳማነት፣ ጨዋማነት እና የውሃ አዘልነት ባህሪያትና ሃብት የለየና ታሳቢ ያደረገ ተደርጎ እንዲጠበቅ ይደረጋል፣
- ➔ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም እና የሰውን ጉልበት በማቀናጀት ሜካናይዝድ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ➔ የተፈጥሮ ሃብት ልማት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አካታች እና አሳታፊ በማድረግ፤ በጋራ ባለቤትነትና በተጠያቂነት የሚጠቀሙበትና የሚያስተዳድሩት፣ ልማቱንም ለገቢ ማስገኛ እና ለኑሮ ዋስትና የሚያውሉት እንዲሆን ይደረጋል፣
- ➔ የብዝሃ-ህይወት ጥበቃና አጠቃቀም እንዲጎለብት ይደረጋል፣
- ➔ የአገር በቀል ዝርያዎች(landraces)እንዳይጠፉ ለመጠበቅ የሚያስችል የዘረመል(ጂን)ባንክና የማህበረሰብ ዝርያ ጥበቃ፣ የማባዛትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል::

## 4.2 የቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት አቅርቦት ሥርዓት

የግብርናን ምርት፣ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳዳግ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ ማባዛትና ሥርጭት፣ ጥራቱና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ የግብዓትና የአገልግሎት አቅርቦትና አጠቃቀም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት አቅርቦት ሥርዓት አጠቃቀም የማበረታቻ

ሥርዓት፣ ፍላጎት፣ ምርትና አቅርቦት መከታተያ ሥርዓት መዘርጋት የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳይ እና አቅጣጫዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.2.1 የግብርና ምርምርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት

የግብርና ቴክኖሎጂ የማፍለቅ ስራ በዋናነት በመንግስት እንደሚሰራ በስራ ላይ ያለው ፖሊሲ አቅጣጫ በማስቀመጡ የግል ባለሃብቱ ተሳትፎ ተገድቦ ቆይቷል። የመንግስት የምርምር ተቋማትም ቴክኖሎጂ ማፍለቅ ላይ መስራት እንደሚችሉ ቢመላከትም በዋናነት በውጪ የፈለቁ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ የማላመድ ስራ ላይ እንዲያተኩር በመደረጉ የምርምር አቅማቸው በሰው ኃይል፣ በመሠረተ-ልማት እና አጠቃላይ የአቅም ግንባታ ስራ ላይ የተሰራው ስራ ውስንነት ነበረበት። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

- ➔ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ የሚያፈልቃቸው ቴክኖሎጂዎች የግብርና ሥነ-ምህዳርን ያማከሉ፣ የገበያ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እና ችግር ፈቺና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ተገቢው ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን በተለይም ባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- ➔ ሁሉን ተዋንያን ማሳተፍና ማቀናጀት፣ የመንግስት ምርምር አቅም እንዲጎለብትና ውጤታማ እንዲሆን፣ የሁሉንም የግብርና ቴክኖሎጂዎችና አሰራር ሥርዓት ያካተተ ምርምር እና የግል ዘርፍን ተሳትፎ የሚያጎለብት እንዲሆን ይደረጋል፣
- ➔ የግብርና ቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ መልቀቅ፣ ደረጃ መመደብ እና መመዝገብ ሁሉንም ተዋንያን አሳታፊ ባደረገ መልኩ የሚመራ ሲሆን የሁሉንም የግብርና ቴክኖሎጂዎች እና የአሠራር፣ የአመራረት ወይም የምርምር ስልቶች እንዲመዘገቡ ይደረጋል፤
- ➔ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎና ኢንቨስትመንት አበረታች እና የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች በብዛትና በዓይነት እንዲጨምሩና ይበልጥ ችግር ፈቺና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ አሰራሩም በገለልተኛ ተቋም ይመራል፣
- ➔ የሁሉም ተዋንያን ምርምሮችና ፈጠራዎች ይደገፋሉ፣ የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች የአዕምሮ ንብረት የባለቤትነት ጥበቃ የሚደረግላቸው ይሆናል፣ የግብርና ቴክኖሎጂ አፍላቂዎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት የሮያሊቲ ክፍያ እንዲያገኙ ይደረጋል።

### 4.2.2 የግብርና ኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት

የኤክስቴንሽን እና ምክር አገልግሎት የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የእውቀት፣ ክህሎት፣ የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተለያዩ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችና ሥልቶችን በመጠቀም የማስተማር፣ የማማከር፣ የማደራጀትና የማስተባበር አገልግሎቶችን መስጠት ነው። ይህ አገልግሎት ገበያ ተኮር፣ ምሉዕ፣ ተደራሽ፣ ዘላቂ፣ አሳታፊ እና ፍላጐት ላይ መሠረት ያደረገ የግብርና ልማትን በማሳካት

የተጠቃሚውን ህይወት ማሻሻልና ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ቁልፍ መሣሪያ ነው።

ይህንንም በመገንዘብ መንግስት ላለፉት ዓመታት በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት እያቀረበ ይገኛል። ይህ አገልግሎት ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና ግብዓቶችን በማስተዋወቅና ተጠቃሚ በማድረግ ጉልህ ሚና ተጫውቷል። ይሁን እንጂ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ ጥራቱን የጠበቀ እና በአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ህይወት ላይ የሚፈለገውን ውጤትና ለውጥ ማምጣት አልቻለም። በመሆኑም በቀጣይ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት የተለያዩ ተዋንያን የሚሳተፉበት፣ ጥራትን ማዕከል ያደረገ፣ አማራጭ፣ ተወዳዳሪና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ በተጠቃሚው ፍላጐት ላይ የተመሠረተ፣ ተደራሽነት ያለው፣ አሳታፊ የሆነ፣ የእሴት ሰንሰለትን መሠረት ያደረገ፣ ምሉዕ እና አካታች እንዲሆን ይደረጋል፣
- የመንግስት የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎትን ተወዳዳሪና ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- የብዙ ተዋንያን የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ ተዋንያን የምዝገባ፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና የአገልግሎቱ ጥራትና ቁጥጥር ስራዎችን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል።

## 4.2.3 የእፅዋት ልማትና ጥበቃ ግብዓቶች

የአፈርን ለምነትና ጤንነትን ለማሻሻል የሚያግዙ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የቅድመና ድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ የምርት እና ምርታማነት እድገትን እንዲጨምር በማድረግ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ግብዓት አቅርቦት፣ የእፅዋት ዘር ሥርዓት፣ የእፅዋት ጥበቃ ግብዓት እና አገልግሎት የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳይ እና አቅጣጫዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.2.3.1 የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ግብዓቶች

የአፈርን ለምነትና ጤንነትን ማሻሻያ ግብዓቶች የምርት እና ምርታማነት እድገት እንዲጨምር ለማድረግ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና በማዕድንና በንጥረ-ነገር የበለፀገ ምርት ለማምረት ጉልህ ሚና አላቸው። መንግስት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትን ለመደገፍ የማዳበሪያ ማምረትና ንግድ የህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ እንዲውል አድርጓል። ይሁንና እስከ አሁን ድረስ ይከናወን የነበረው የአፈር ማዳበሪያን ከውጪ አስገብቶ በመንግስት እና በህብረት ስራ ማህበራት አማካኝነት ማሰራጨት ነበር።

በሌላ በኩል የአፈር ለምነትን፣ ሥርዓተ-ምህዳርን እና የተጠቃሚውን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የማዳበሪያ ፍላጎትን ለማሰባሰብና ለማጠናከር የሚረዳ ሥርዓት ካለመኖሩም ባሻገር በውስን ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ዓይነት ላይ ብቻ በመወሰን እና ለሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ግብዓቶች በተለይም ለተፈጥሮ ማዳበሪያ፣ የግብርና ኖራ እና ጅብሰም ትኩረት አለመስጠት በሀገር ደረጃ ለተመዘገበው አነስተኛ የማዳበሪያ አጠቃቀም ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው። በተጨማሪም የማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት ሥርዓት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ አለመሆን፣ እሴት የማይጨምሩ ተዋንያኖች መብዛት፣ በቂና የተቀላጠፈ የሎጂስቲክስ አቅርቦት እጥረት ምክንያት ተጠቃሚዎች ማዳበሪያን በሚፈልጉበት ወቅትና ጥራት ያለማግኘት፣ ለዘርፉ በቂ የብድር አቅርቦት እና ጠንካራ የብድር አመላለስ ሥርዓት አለመዘርጋት የዘርፉ ዋነኛ ተግዳሮቶች ናቸው። ከዚህ አንፃር እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ግብዓት አቅርቦት ለማሻሻል የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ➔ የአፈር ለምነትና ጤንነት ሥርዓተ-ምህዳርን እና በተጠቃሚው ፍላጎት ላይ እንዲመሠረት ይደረጋል፣
- ➔ ማዳበሪያን ከውጭ ከማስገባት ይልቅ አገር ውስጥ ማምረት እና የሀገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልቶ ወደ ውጭ መላክ፣ በተወሰኑ ሰው ሰራሽ የማዳበሪያ አይነቶች ላይ ከማተኮር ይልቅ ሥርዓተ-ምህዳርን መሠረት ያደረገ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ላይ ትኩረት ይደረጋል፣
- ➔ ማዳበሪያ ማምረት፣ አቅርቦትና ግብይት ውስጥ የግል ባለሃብቱና የህብረት ስራ ማህበራት ሚና እንዲያድግ ይደረጋል፣
- ➔ ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ በማምረት ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ይደረጋል፣
- ➔ የአርሶ አደሩን የመግዛት አቅም ለማሳደግ የማዳበሪያ ብድር አገልግሎት የማቅረብ እና የብድር አመላለስ ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ ጠንካራ የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓቶች ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.2.3.2 የእፅዋት ዘር ሥርዓት

ጥራቱን የጠበቀ የተሻሻለ የእፅዋት ዘር መጠቀም ለምርትና ምርታማነት እድገት ወሳኝ ግብዓት ነው። ይህንኑ በመገንዘብ መንግሥት የእፅዋት ዘር ፍላጎትን ለማሟላት በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ቢሆንም ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሆነና ተዓማኒነት ያለው የዘር ፍላጎትና አቅርቦት ማሰባሰቢያና ማጠናቀሪያ ሥርዓት አለመኖር፣ ያለውም ሥርዓት ቢሆን በውስን ሰብሎችና ዝርያዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ ለሌሎች ሰብሎችም ሆነ አዳዲስ ለሚለቀቁ ዝርያዎች አሰራር ባለመዘርጋቱ፣ ዘር አምራቾች በግብይት ሥርዓቱ ላይ ያላቸው ሚና አነስተኛ መሆኑ እና የዘር ግብይት መሠረተ-ልማት በበቂ ሁኔታ አለመደራጀቱ እና የዘር ጥራት

ማረጋገጥ እና የኳራንታይን አሰራሩም አለመጠናከር የዘር ኢንዱስትሪውን ጎድቶት ቆይቷል። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ➔ የእፅዋት ዘር አቅርቦት ሥርዓተ-ምህዳርን እና የተጠቃሚውን ፍላጎት መሠረት ያደረገና አቅርቦቱም አስተማማኝ እንዲሆን፣ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልቶ ወደ ውጭ መላክ የሚያስችል አቅም ይፈጠራል፣
- ➔ የምርጥ ዘር አቅርቦትና ግብይት በገበያ መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፣ የግል ባለሃብቱንና የህብረት ስራ ማህበራት ሚና እንዲጎላ ይደረጋል፣ ዘርፉንም በተቀናጀ መልክ ለመምራት ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል፣
- ➔ ጠንካራ የእፅዋት ዘር ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይገነባል፣
- ➔ የመንግስት ምርጥ ዘር ድርጅቶች በዘር ኢንዱስትሪው ሊጫወቱት የሚገባውን ሚናና ኃላፊነት ተለይቶ ማሻሻያ ይደረጋል።

### 4.2.3.3 የእፅዋት ጥበቃ ግብዓትና አገልግሎት

ሰብልን ከተባይ፣ ከበሽታ አምጪ ተህዋስያን እና ከአደገኛ ወራሪ አረሞች ጥቃት መከላከል የቅድመና ድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ ምርትን ለመጨመር ብሎም የመዳረሻ ገበያዎች የምርት ጥራት መስፈርትን ለማሟላት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጠቀም ዋነኛ የሰብል ጤና ጥበቃ ዘዴ ሆኖ ይገኛል። መንግስት የፀረ-ተባይ ኬሚካል ምዝገባና ቁጥጥር የህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ አውሏል። ይሁንና በስራ ላይ ያለው የህግ ማዕቀፍ አንድ የተመዘገበን ፀረ-ተባይ ኬሚካል የመጀመሪያው አስመጪ ሳይፈቅድ በሌላ አስመጪ ወደ ሀገር ለማስገባት እንደሚቻል በግልፅ ባለመደንገጉ፣ በሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው በመስራት ላይ ያሉ አለም አቀፍ አምራቾች የራሳቸውን የተመረተ (በፓተንት የተመዘገበ) ፀረ-ተባይ በሀገር ውስጥ ለማስመዝገብና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ስራ እንዲሰሩ የማያበረታታ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሸግ እና ዳግም ለማሸግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ባለማካተቱ ምክንያት የግሉን ዘርፍ እና የህብረት ስራ ማህበራትን በፀረ-ተባይ አቅርቦትና ግብይት ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል። ሌላው የነባሩ ፖሊሲ ትኩረት ፀረ-ተባይ ከውጪ አስገብቶ ማሰራጨት ሲሆን የርጭት ስራውም የሚከናወነው በተነፃፃሪ የጤናና የአካባቢ ጉዳትን የሚቀንሱ አማራጭ የተባይ መከላከያ መንገዶችን የሚያበረታታ አልነበረም። በተጨማሪም ሀገሪቱ ያላት ፀረ-ተባይ ኬሚካል የመቆጣጠር አቅም ውስን እንዲሆን እና ፀረ-ተባይ ኬሚካልን በወቅቱ ለማስወገድ ባለመቻሉ ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉና ጊዜ ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካል ክምችት እንዲፈጠር አስገድዷል።

በተጨማሪም መንግስት ለተወሰኑ ተባዮች የቅኝት፣ አሰሳ፣ ክትትል፣ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የእፅዋት ተባይ ልየታና ትንተና፣ ድህረ-ምርት ተባይ መከላከል ሥርዓት ዘርግቶ የመከላከልና የቁጥጥር ስራዎች እያከናወነ ይገኛል። ይህንን ለማገዝ በተለያየ ጊዜና ደረጃ የሰብል ጤና ክሊኒኮችና የምርምር ስራዎች ተሰርተዋል። ሆኖም ግን በአየር ንብረት ለውጥ እና ሌሎች ምክንያቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋና

እየጨመረ የመጣውን የተባዮች ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እና የመሠረተ-ልማት ክፍተት ይታያል። የሰብል ጥበቃ ስራ በተጠናከረ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር ባለመመራቱ የዘርፉ ተዋንያን እና መሠረተ-ልማትን በአግባቡ መጠቀም አልተቻለም። በተለይም ለእፅዋት ጤና ክሊኒኮች የተሟላ መሠረተ-ልማት ባለመኖሩ ተልዕኮዎቻቸውን ለመወጣት ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል። በተመሳሳይም የሰብል ጥበቃ አገልግሎት እንደ አንድ የአገልግሎት ዘርፍ እንዳይስፋፋ እንቅፋት ሆኗል። ይህም አርሶ አደሩን በበቂ ሁኔታ በመደገፍ በነፍሳት ተባይ፣ በበሽታና አረም የሚደርሰውን ጥቃት በመከላከል ምርትና ምርታማነትን በሚለፈገው መጠን ለማሳደግ አልተቻለም። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

- ➔ የድንበር ዘለል ተዛማችና መደበኛ ተባዮችን አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚያስችል የተባይ ቅኝት፣ አሰሳ፣ ክትትል፣ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቅያ ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የእፅዋት ጥበቃ ግብዓት አቅርቦትን በበቂ መጠንና ዓይነት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሸግ እና ዳግም ለማሸግ የሚያስችል አቅም በመፍጠር የሀገር ውስጥ ፍጆታን አሟልቶ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- ➔ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ጠንካራ የምዝገባ፣ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ግብይቱና ስርጭቱ በገበያ መርሆዎች እንዲመራ ይደረጋል፣
- ➔ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም የጤና እና የአካባቢ ጉዳት እንዲቀንስ ይደረጋል፣ ጥቅም ላይ የማይውሉ ጊዜ ያለፈባቸው የፀረ- ተባይ ክምችት እንዳይፈጠር እና ተፈጥሮ ሲገኝ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፣
- ➔ የመንግስትየ ፀረ-ተባይ ኬሚካል አምራች ድርጅቶች በዘርፉ ሊጫወቱት የሚገባውን ሚናና ኃላፊነት ተለይቶ ማሻሻያ ይደረጋል፣ እንዲሁም የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- ➔ የእፅዋት ጤና አጠባበቅ፣ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥርዓት (የተቀናጀ የተባይ በሽታን መከላከያ መንገዶችን ጨምሮ) እንዲጠናከር ይደረጋል፣ የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀትና መሠረተ-ልማት ይገነባል።

### 4.2.4 የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማትና ጤና ጥበቃ ግብዓቶች

ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የእንስሳትና ዓሳ ዝርያና ዘር እና የእርባታ ግብዓት አቅርቦት፣ የእንስሳት መኖ ልማት፣ ዝግጅትና አቅርቦት፣ እንዲሁም የእንስሳትና ዓሳ ጤና ጥበቃ ግብዓትና አገልግሎት የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳይ እና አቅጣጫዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 4.2.4.1 የእንስሳትና ዓሳ ዝርያ፣ ዘር እና የእርባታ ግብዓት

የተሻሻሉ የእንስሳትና የዓሳ ዝርያዎችን፣ ተያያዥ የተሻሻሉ ግብዓቶችን መጠቀም፣ የእንስሳትና ዓሳ እርባታን ለማዘመን እና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ወሳኝ ነው። በዚህ ረገድ መንግስት የምርምር እና በሰው ሰራሽ ዘዴ የቀንድ ከብት የማዳቀያ ማዕከላት በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ቢያቋቁምም የእንስሳትና የዓሳ ዝርያዎች ማሻሻል ስራዎች ሥርዓት ባለው መንገድ ባለመመራታቸው የሚፈለገው ውጤት አልተመዘገበም። ይልቁንም የእንስሳትና የዓሳ ዘር ሃብታችንን ባልተፈለገ መንገድ በመበረዝና በመሸርሸር ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም የሀገር ውስጥ የእንስሳት ዝርያዎቻችን በልቅ የእርቢ ሂደት ምክንያት ተፈላጊ ባህርያቸው እየተሸረሸሩና እየተበረዙ በመሄድ ንጹህ የሀገር በቀል የእንስሳት ዝርያ እንዳይጠፋ የሚጠብቅ የህግ ማዕቀፍና አሰራር አልተዘረጋም። በተጨማሪም የንብ እርባታን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦትና ግብይት ሥርዓት አልተዘረጋም። በመሆኑም ያለንን የዘርፉን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ለማዋል የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ➔ የእንስሳትና የዓሳ የውጪ ዝርያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማዳቀልና በሀገር ውስጥ ለማባዛት እና ሀገር በቀል ዝርያዎችን እንደየአግባባቸው በመለየት ለማሻሻልና ለማባዛት የሚያስችል አቅም ይፈጠራል፣
- ➔ የተሻሻሉ የእንስሳትና የዓሳ ዝርያና ዘር አቅርቦትና ግብይት በገበያ መርሆዎች እንዲመራ ይደረጋል፣
- ➔ የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን (የማህበረሰብ አቀፍ - የዝርያ ማሻሻያ) ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- ➔ የመንግስት የዝርያ ማሻሻያ፣ የብዜት እና ማዳቀያ ማዕከላት ውጤታማነታቸውን ለማጎልበት ሚናቸውና ሃላፊነታቸው ተለይቶ ማሻሻያ ይደረጋል፣
- ➔ የንብ እርባታን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦትና ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ ብዝሃ - ህይወትን መሰረት ያደረገ ጠንካራ የጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት፣ ሥርዓቱን አቀናጅቶ የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀት እና መሠረተ - ልማት (የእንስሳት ዝርያና ዘር መረጃ ሥርዓትን ጨምሮ) ይዘረጋል።

#### 4.2.4.2 የእንስሳትና ዓሳ መኖ ልማት፣ ዝግጅትና አቅርቦት

ጥራቱን የጠበቀ መኖ የእንስሳት ሃብት ምርትና ምርታማነት በማሻሻልና ትርፋማ በማድረግ የእንስሳት ሃብት ልማትን ለማዘመን ወሳኝ ግብዓት ነው። ይህንኑ ዕውን ለማድረግ መንግስት የመኖ ልማት እና አቅርቦት ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። የመኖ ልማትና ንግድ አስተዳደርና ቁጥጥር ለማጠናከርና የመኖ ልማቱን ኢንዱስትሪና የእንስሳት እርባታውን በማሻሻል የሕዝብን ጤንነት ለመጠበቅ መንግስት የቁጥጥር

ህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ አውሏል። በተጨማሪም የመኖ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን ዋና ዋና የመኖ ግብዓቶችንና በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምጥን መኖዎችን የደህንነትና የጥራት ደረጃዎች ወጥቶላቸው ወደ ስራ ተግብቷል። ይሁን እንጂ ለመኖ ልማት የሚውሉ መሬቶችን በአግባቡ ለይቶ አለማስቀመጥ፣ እንዲሁም መኖ ማምረትና ለገበያ ማቅረብ እንደ አንድ ወሳኝ የግብርና ዘርፍ አለመታየትና ለማስፋፋት የሚረዳ አበረታች የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የተሻሻሉ የመኖ ሰብሎች፣ የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ-ምርት እና በፋብሪካ የተዘጋጁ መኖዎችን በኮሜርሻል ደረጃ ለማምረት፣ የመኖ አቅርቦትና ግብይት በገበያ መርሆዎች ይመራል፣
- የእንስሳት መኖ ልማት፣ ዝግጅትና አቅርቦት የሀገር ውስጥ ፍጆታን አሟልቶ ወደ ውጭ መላክ እንዲቻል ይበረታታል፣
- የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲው ለመኖ ልማት የሚውሉ መሬቶችን ለመለየት ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል፣ የሬንጅላንድ እና የተፈጥሮ ግጦሽ አያያዝና አጠቃቀም ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ጠንካራ የመኖ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.2.4.3 የእንስሳትና ዓሳ ጤና ጥበቃ ግብዓት እና አገልግሎት

የእንስሳት በሽታ አምጪ ተህዋስያንና በሽታ አስተላላፊ ተባዮችን ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሃኒትና ክትባት ተጠቅሞ ለመከላከል እና ለማከም የእንስሳት ሃብት ልማትንና ጤንነት አጠባበቅን ለማሻሻል፣ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እና የህብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅ የእንስሳት ጤና ግብዓት ወሳኝ ነው። ይህንንም ፍላጎት ለማሟላት የእንስሳት ክትባት በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማሳደግ የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በማቋቋም የእንስሳት በሽታን ለማከም ብሎም ለመከላከል ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በተጨማሪም የውጪ ምንዛሬ በመመደብ የእንስሳት መድሃኒት ከውጪ ማስገባት እንዲሁም የእንስሳት መድሃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ ዘርግቶ አቅርቦቱን ሲደግፍ ቆይቷል።

የእንስሳት መድሃኒት አቅርቦት የበሽታ ስርጭት፣ የእንስሳት ብዛት እና ወቅትን መሠረት ያደረገ የትንበያ ሥርዓት የሚከተል ባለመሆኑ በተጠቃሚው የሚፈለጉ መድሃኒቶችን በበቂ መጠንና ዓይነት ከውጪ ለማስገባት፣ በሀገር ውስጥ ለማምረት እና ለማቅረብ አልተቻለም። በአነስተኛ መጠን የሚፈለጉ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የተመዘገቡ ወይም ያልተመዘገቡ መድሃኒቶችን ለማስገባት የሚያስችል የማበረታቻና አሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ በገበያ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እጥረት እንዲከሰት አድርጓል። የእንስሳት በሽታን ለመመርመር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ

ባለመሟላታቸው ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የእንስሳት መድሃኒት በመጠቀም በአለም በከፍተኛ ደረጃ ስጋት የሆኑ ተህዋስያን መድሃኒትን እንዲላመዱ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

በተጨማሪም የእንስሳት መድሃኒት አቅርቦት በውስን አምራቾች ብቻ የሚቀርብ በመሆኑ አብዛኛው ከውጪ የሚገቡ መድሃኒቶች ላይ ያተኮረ ሆኗል፡፡ ሆኖም ግን በውጪ ምንዛሬ እጥረት መድሃኒት በሚፈለግበት ወቅት፣ ዓይነትና መጠን ለማቅረብ አልተቻለም፡፡ በተመሳሳይም የክትባት እና መድሃኒት ማምረትና ማቅረብ በአንድ የመንግስት ድርጅት ብቻ የሚከናወን በመሆኑና ይህም ቢሆን በተወሰኑ ምርቶች ላይ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልቶ ወደ ውጭ የመላክ አቅም ቢፈጠርም በዓይነትና በጥራት የማምረት የአቅም ውስንነት አለበት፡፡ በሌላ መልኩ ለባህላዊ የእንስሳት ህክምና ዘዴ የአሰራር ሥርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ባለመዘርጋቱ ለእንስሳት ህክምና ያለውን አስተዋጽዖ በተሻለ መልኩ መጠቀም አልተቻለም፡፡

እንዲሁም የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሥርዓት የመንግስትና የግሉን ዘርፍ ሚዛናዊና አግባብ ባለዉ መልኩ ያላሳተፈና አገልግሎቱ በአብዛኛው በመንግስት እንዲቀርብ አድርጎታል፡፡ ሆኖም ግን ደረጃውን የጠበቀ፣ ተደራሽ እና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችል እንዲሁም እያደገ እየመጣ ያለውን ዘመናዊ ስልተ - ምርቶችን ያማከለ የእንስሳት ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ፡፡

- ➔ የእንስሳት መድሃኒት፣ ክትባት እና የህክምና መሳሪያ አቅርቦትን በበቂ መጠንና ዓይነት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለማምረት እና የሀገር ውስጥ ፍጆታ አሟልቶ ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል አቅምና ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- ➔ የእንስሳት መድሃኒት፣ ክትባት እና የህክምና መሳሪያ አቅርቦትና ግብይቱ በገበያ መርሆዎች ይመራል፣ እንዲሁም ጠንካራ የምዝገባ፣ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይገነባል፣
- ➔ የገበያ ጉድለት ለሚስተዋልባቸው የመድሃኒትና ክትባት አይነቶች አቅርቦትና የፋይናንስ አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን ተሳትፎ ለማሳደግ የአስቻይ ሁኔታና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲሁም የመንግስት እና የግል አጋርነት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ ጥቅም ላይ የማይውሉ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድሃኒት ክምችት እንዳይፈጠር እና ተፈጥሮ ሲገኝ በወቅቱም ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የእንስሳት ጤናና ደህንነት አገልግሎት ተዓማኒ፣ ተደራሽ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተወዳዳሪ እንዲሆን የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ ሚናና ኃላፊነት በአግባቡ ተለይቶ ይተገበራል፣

- ➔ የእንስሳት ጤናና ደህንነት አገልግሎት ለማቅረብ የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ ሚናና ኃላፊነት በግልፅ የሚለይ ፍኖተ-ካርታ ይነደፋል፣ ቅንጅታዊ አሰራርና መሠረተ-ልማት ይዘረጋል፣ እንዲሁም የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራት ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- ➔ የበሽታ መከላከል፣ መቆጣጠር፣ የመረጃ ቅብብሎሽ እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ (የድንበር ዘለል በሽታዎችን ጨምሮ) ሥርዓት ማዘመን እንዲሁም የአገልግሎቱ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.2.5 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሥርዓት

የሜካናይዜሽን አገልግሎት የግብርና ልማትን ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ ሰብልና እንስሳት ምርት ማምረት፣ መሰብሰብ፣ ማቀነባበር፣ ማጓጓዝ እና ማሸግ በተሳለጠ ሁኔታ በማከናወን የሰው ኃይል፣ የመሬትና የሌሎች ግብዓቶችን ምርታማነት በመጨመር፣ ቅድመና ድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ እና የምርት ጥራት ለማሻሻል እና የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ለመጨመር ወሳኝ ነው። የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን አቅርቦት ለማሻሻል እና የአገልግሎት አሰጣጡን ለማስፋፋትና ተደራሽ ለማድረግ ለተወሰኑ ቴክኖሎጂዎችና መሳሪያዎች ከቀረጥ ነጻና ታክስ እፎይታ ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ ከውጪ የሚገቡትም ሆነ በሀገር ውስጥ እየተመረቱ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ጥራትና ደረጃ ማሟላታቸውን የሚቆጣጠር የአሰራር ሥርዓት በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ➔ የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለማልማትና ለማባዛት እንዲሁም ከውጭ ለማስገባት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጠራል፣
- ➔ የግል ባለሃብትና የህብረት ስራ ማህበራት የመሪነት ሚና እንዲኖራቸው የሚያበረታታና የሚያመቻች፣ ቀልጣፋ የማስተዋወቅ፣ የሽያጭ እና የድህረ-ሽያጭ አገልግሎት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- ➔ ጠንካራ የአጠቃቀምና የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል እንዲሁም አጋዥ መሠረተ-ልማት ይገነባል።

### 4 .2 .6 የቴክኖሎጂ እና ግብዓት አጠቃቀም የማበረታቻ ሥርዓት

የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለዉ የቴክኖሎጂና የግብዓት አጠቃቀም ማሳደግ ወሳኝ ድርሻ አለው። ይሁንና በአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር ላይ የተመሰረተው የሀገራችን ግብርና የግብዓትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ነው። ይህም የሀገራችን አርሶና አርብቶ አደሮች ምርቶች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ አድርጓል። ከዚህ አንጻር የሚከተለው የፖሊሲ አቅጣጫ ተግባራዊ ይደረጋል።

- ➔ የግብርና ቴክኖሎጂዎችና ግብዓት አጠቃቀምን ለማሳደግ የአርሶና አርብቶ አደሩ እና የከተማ ግብርና ተዋንያን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ፣ በጥናት ለሚለዩ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶች ላይ የገበያ ሥርዓቱን በማያዛባ ሁኔታ እና በጊዜ የተገደበ ማበረታቻ ይሰጣል።

### 4.2.7 የግብዓት ፍላጎት፣ ምርት እና አቅርቦት መከታተያ ሥርዓት

የግብርና ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን ማስፋፋትና ተደራሽ ማድረግ የሰብል እና የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ይህንን በመገንዘብ መንግስት የተለያዩ ስራዎችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ሆኖም የፍላጎት ፈጠራና ዳሰሳ የሚካሄድላቸው ግብዓቶች ውስን ከመሆናቸውም በተጨማሪ ፍላጎቱ የሚሰበሰብበት መንገድ የመረጃ ተአማኒነት የጎደለው ሆኖ ይገኛል። በዚህ ሁኔታ የቀረበው ግብዓት በዓይነትም ሆነ በመጠን ከተጠቃሚው ፍላጎት ጋር አለመጣጣም፤ ማለትም የመጠን ማነስ ወይም መብዛትና ጥቅም ላይ ሳይውል ማደርን አስከትሏል። የተጠቃሚውን የግብዓት ፍላጎት በጊዜ፣ በጥራት፣ በዋጋና የአካባቢ ነባራዊ ሁኔታዎችን በተሟላ መልኩ በማገናዘብ ለማቅረብ ለግብዓቶቹ ያለው የፍላጎት መጠን፣ የሚኖረውን የምርት መጠን እና የአቅርቦቱን አጠቃላይ ሁኔታ መከታተል የሚያስችልና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሆነ የተሟላ ሥርዓት አልተዘረጋም። የተዘረጉትም በሙከራ ደረጃ ያሉና የተወሰኑ ግብዓቶችን ብቻ ያካተቱ እና ውስን ተጠቃሚዎች ተደራሽ የሆኑባቸው ናቸው። ከዚህ አንጻር የሚከተለው የፖሊሲ ጉዳይ ተግባራዊ ይደረጋል።

- ➔ የተቀናጀ የግብዓት ፍላጎት፣ ምርትና አቅርቦት መከታተያ የሁሉንም ግብዓቶች ተጠቃሚዎች (ሰፋፊ ግብርና አልሚዎችን ጨምሮ)፣ አምራቾች እና አቅራቢዎችን ያካተተ እና በኢንፎርሜሽን ግንኙነት ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖ ይገነባል።

## 4.3 የግብርና ውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር

ግብርናን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ በፍጥነት እያደገ የመጣውን ህዝብ የምግብ ፍላጎት ለማሟላት፣ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖን ለመቋቋም ዘላቂነት ያለው የመስኖ ልማት እና የግብርና ውሃ አጠቃቀም ማሻሻል ቁልፍ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ ባለፉት ዓመታት ዘላቂ የውሃ አጠቃቀምን መሠረት በማድረግ የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ማህበረሰቡ ከዝናብ ጥገኝነት እንዲላቀቅ ጥረት ተደርጓል።

ይሁን እንጂ ሁሉንም የውሃ አማራጮች ታሳቢ ያደረገ ስራ ባለመሰራቱ በመስኖ የለማው መሬት መልማት ከሚችለው አንፃር አነስተኛ ነው። በተለይም በሀገራችን እምቅ የከርሰ-ምድር ውሃ ሃብት ሥራ ላይ ለማዋል ደጋፊ የሆነ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቅረፅ እና ሥርዓት በመዘርጋት ዘመኑ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች በስፋት በመጠቀም ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የመስኖ እርሻን በማስፋፋት

ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ አልተቻለም። በተጨማሪም የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር መሠረት ያደረገ የግብርና ውሃ ምርምር ደካማ መሆኑና የልማት ኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት አለመቀናጀት የቴክኖሎጅና የተሻሻለ የግብርና ውሃ አሠራር ሥርዓትን ደካማ አድርጎታል። ስለሆነም ውጤታማ የግብርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችሉ የሚከተሉት አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

- ➔ የግብርና ውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ለገፀ-ምድር፣ ዝናብና ከርሰ-ምድር ውሃ ምንጮች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በተሻለ ሁኔታ እንዲለማ ይደረጋል፣
- ➔ የዝናብ ውሃ አሰባሰብና አጠቃቀም እንደዋና የውሃ አቅርቦት አማራጭ ተደርጎ በትኩረት ይሰራል፣ የውሃው ምንጭ በሆኑ ተፋሰሶች ልማት ጋር በቅንጅት እንዲሰራ ይደረጋል፣
- ➔ የከርሰ-ምድር ውሃ ልማትና አጠቃቀም ሌላኛው የውሃ አቅርቦት አማራጭ ተደርጎ በትኩረት ይሰራል፣ የውሃው ምንጭ በሆኑ ተፋሰሶች ልማት ጋር በቅንጅት እንዲሰራ ይደረጋል፣
- ➔ የግብርና ውሃ አጠቃቀም የዓሳ ልማትን እንዲደግፍ ይደረጋል፣
- ➔ ሰው ሰራሽ የግብርና ውሃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተለይ በቆላማ አካባቢዎች ለማስፋት የድጋፍና የልማት ፕሮግራም ይዘረጋል፣
- ➔ የግብርና ውሃ አያያዝ የውሃና ኃይል ማቅረብና ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን አቅርቦት የሚያበረታታ እንዲሆን ይደረጋል፣ የምርምርና ኤክስቴሽን አገልግሎት በትኩረት ይቀርባል፣
- ➔ የተጠናከረ የመስኖ መሠረተ-ልማት የርክክብ፣ ኦፕሬሽንና አስተዳደር እንዲኖር ይደረጋል፣ ይህም ከተፋሰስ ልማት ጋር እንዲቀናጅ ይደረጋል፣
- ➔ የመስኖ ልማትና አስተዳደር ፋይናንስ አማራጮችን እንዲሰፉ ይደረጋል፣ የግሉ ዘርፍ እና የህብረት ስራ ማህበራት የሚኖራቸው ሚና እንዲያድግ ይደረጋል፣
- ➔ የመስኖ ተጠቃሚዎች የአውታሩን አስተዳዳራዊ ወጪ እንዲጋሩ ይደረጋል፣
- ➔ የመስኖ ልማት ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል፣
- ➔ የሁሉንም ዓይነት መስኖ አውታሮች ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም የሚመራ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል።

## 4.4 የምርት ግብይት

በገበያ የተመራ ግብርና ልማት የግብርና ስራን እንደ ቢዝነስ ተግባር የማጤን እና አምራቾች የምርት ስራን ከመጀመራቸው አስቀድሞ ገበያን የማወቅ፣ ምን ዓይነት ምርት፣ በምን መጠን፣ ጊዜ፣ ዓይነት እና የጥራት ደረጃ እንደሚፈለግ አውቆ ለማምረት ያስችላል። ይህም የገበያ ሥርዓት የበለጠ መዋቅራዊ፣ በእዉቀትና

በመረጃ ላይ የተመረኮዘ እና ግልጽ እንዲሆን የሚረዳ በመሆኑ አምራቹ በምርቱ መሸጫ ዋጋ ላይ የውሳኔ ሰጭነት ሚና እንዲኖረው በማድረግ ለሚያመርተው ምርት የተሻለ የገበያ ዋጋ እና ገቢ ያስገኛል። የግብይት ሥርዓትን በቀጣይነት ለማሻሻልና ለማጠናከር የሀገር ውስጥ ምርት ግብይት፣ የወጪ ንግድ እና የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት የገበያ አሰራር እና የህብረት ስራ ማህበራትን ማዘመን የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ መዘርጋት ያስፈልጋል።

### 4.4.1 የግብርና ምርቶች ግብይት

ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ፍትሃዊ የሆነ የግብርና ምርት ግብይት ሥርዓት ማስፈን አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮች ትርፋማ ወደ ሆኑ አመራረቶችና ምርቶች እንዲሸጋገሩና የኑሮ ደረጃቸው እንዲሻሻል፣ ሸማቹም ጥራት ያላቸውን ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ እና ጥራቱን የጠበቀና ቀጣይነት ያለው ምርት ለወጪ ንግድ ለማቅረብ ያግዛል። ሆኖም ግን የምርት ግብይት የአሰራር ሥርዓት በተሟላ መልኩ ባለመዘርጋቱ፣ በግብይት ሰንሰለቱ እሴት የማይጨምሩ ተዋንያን በመበራከታቸው ከፍተኛ የግብርና ምርት ዋጋ መዋዠቅ፣ የምርት አቅርቦትና ጥራት አስተማማኝ እንዳይሆን አድርጎታል። በተጨማሪም ኢንዱስትሪዎች በዋናነት አስፈላጊውን የግብርና ምርት ባለማግኘታቸው ከአቅማቸው በታች ለማምረት ተገደዋል። የግብርና ምርቶች ግብይት የህግ ማእቀፎች እና አሰራር ሥርዓት አምራቹ ተገቢውን የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ አላስቻሉም። ከዚህም በላይ የተወሰኑ የግብርና ምርቶችንም አምራቹ ከማምረቻና ተዛማጅ ወጪዎች በታች እንዲሸጥ አስገድዶታል። የገበያ ቁጥጥር ሥርዓት የተሟላ አለመሆኑ የጥራት ደረጃዎች፣ የምርት ዱካና የምግብ ደህንነትን፣ የተዋንያን የግብይት አሰራር ሁኔታ እና የምርትና ገንዘብ ልውውጥ እንዲሁም የምርት ትራንስፖርት አገልግሎት የተቀላጠፈ አለመሆን የግብርና ምርት ግብይት እንዳይዘምን አድርጎታል።

የግብይት ፋይናንስና ስጋት መድን ሽፋን የተሟላ አለመሆን፣ የግብርና ምርትን በማሰባሰብ፣ በማከማቸት እና ጥራቱን በመጠበቅ ቀጣይነት ያለው የምርት አቅርቦት ለማከናወን ከፍተኛ የሆነ የመግዣ እና የመሠረተ-ልማት ፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ሌላው በግብርና ምርት ግብይት አስራር ላይ ያለ ክፍተት ነው። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

- ➔ የግብርና ምርቶች ግብይት የምርት ዓይነትና የገበያ መዋቅርን በለየ፣ እሴት ሰንሰለቱን በተከተለ እና የጥራትና ድህረ-ምርት ብክነት መቀነስ እንዲያስችል ሆኖ ይገነባል፣
- ➔ የምርት ግብይት በጥራት ደረጃ ላይ የተመሰረተ የዋጋ ትመና እንዲሰፍን ይደረጋል፣ የገበያ መረጃ አቅርቦት እና ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት እንዲሁም ኤሌክትሮኒክ ግብይት፣ ዘመናዊ የግብይት መድረኮችንና አገልግሎቶች ይገነባል፣

- ➔ የምርት የመሸጫ ዋጋ የማምረቻና ተዛማጅ ወጪዎችን የሚመልስ እንዲሆን በጥናት በሚመረጡ የግብርና ምርቶች በጊዜ የተገደበና ከገበያ መርሆች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለአምራቾች ዝቅተኛ የምርት ዋጋ ድጋፍ ይደረጋል፣
- ➔ የግብርና ምርት በውል ማምረት፣ በመጋዘን ደረሰኝ ሥርዓት፣ ፎርዋርድ ውል (forward contract) እና ፊውቸርስ ገበያ (futures market) እንዲመሠረት ይደረጋል፡፡

### 4.4.2 የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ አቅርቦትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ

የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ለሀገራችን ዋነኛ የውጪ ምንዛሬ ምንጭ፣ ግብርናን ገበያ-መር እንዲሆን ማስቻል እና በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የወጪ ንግድን ለማበረታታት የግብርና የቀረጥ እፎይታ፣ የብድር አቅርቦትና አነስተኛ የወለድ ምጣኔ፣ የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት እና ለአልሚዎች መሬትን በዝቅተኛ የሊዝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ የማበረታቻ ዕርምጃዎችን መንግስት በመውሰድ የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ እድገት ቢያሳይም ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ያለው ድርሻ ሲታይ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የግብርና የወጪ ምርቶች ልማት እና ንግድ የፖሊሲ ማዕቀፍ የወጪ ንግዱን የምርት አቅርቦት መጠንና ዓይነት የሚለይ፣ ለጥራትና ዕሴት ጭመራ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ፣ የገበያ ማስፋፊያ ስራዎችን ለማከናወን፣ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማስፋትና የዋጋ ተወዳዳሪነትን ለማሳዳግ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ በመሆኑም የገዢ ሀገሮችን የተለያዩ የጥራት እና ደህንነት መስፈርቶችን ለይቶ አለመዘጋጀት፣ የዓለም ዓቀፍ ገበያን መሠረት ያደረገ የምርት ትንበያ መረጃ ሥርዓት አለመኖር፣ በንግድ ድርድር የተገኙ እንዲሁም በሀገራትና አህጉራት ችሮታ የተሰጡ የገበያ እድሎችን አሟጦ አለመጠቀም፣ ምርቶቻችን ብራንድ አለመደረጋቸው ከግብርና ወጪ ንግድ ሊገኝ ይችል የነበረውን የበለጠ ውጭ ምንዛሬ ማግኘት አልተቻለም፡፡

የሆርቲካልቸር ምርት የወጪ ንግድ መጠን ለማሳደግ ከአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ምርት ለማሰባሰብ (አግሪጌሽን) የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረግ፣ ምርት አሰባሳቢዎች ኤክስፖርት በሚደረገው ምርት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የሚጠይቅ በመሆኑ አነስተኛ አርሶ አደሮች ለወጪ ንግድ አቅርቦት ተሳትፎን እየገደበ ይገኛል፡፡ የግብርና ምርቶች ከሀገር እንዳይወጡ እገዳ ለመጣል መነሻ የሚሆኑ ኢኮኖሚያዊና የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም እገዳ ከመጣሉ በፊት አምራቾችና የገበያ ተዋናዮች እና ከመንግስት አካላት ጋር የሚደረግ በቂ ውይይት አለመኖሩ እንዲሁም የእገዳ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ በውሳኔው ሊጎዱ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት ውሳኔውን ሊያውቁ የሚችሉበት ግልፅ አሰራር አልተዘረጋም፡፡ ስለሆነም የወጪ ንግድ ውጤታማ ለማድረግ የሚከተሉት አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

- ➔ የግብርና ወጪ ምርቶች ልማትና ንግድ የምርት ዓይነትና መጠን፣ የመዳረሻ ገበያ ፍላጎት (የደን መጨፍጨፍና መራቆትን የተከለከለ የግብርና ምርት ሥርዓት የሚጠይቁትን ጨምሮ)፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪነትን የለየና እሴት ሰንሰለቱን የተከተለ ሆኖ ይገነባል፣
- ➔ የግብርና ምርቶች ከሀገር እንዳይወጡ የሚወሰንበት አሰራር ሥርዓት ግልፅና ተገማች እንዲሆን ይደረጋል፣
- ➔ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስምምነቶች የሚከፍቱትን የገበያ እድል በበለጠ ለመጠቀም የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ለማሳደግ ይሰራል፣
- ➔ የግብርና ወጪ ምርቶች ልማት እና ንግድን አቀናጅቶ የሚመራ ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል።

### 4.4.3 ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት

ሀገራዊ የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት በግብርና ዘርፍ ላይ ትኩረት በማድረግ ዋና ዋና የምግብ ሰብሎችና የእንስሳት ውጤቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት በምግብ ራስን በመቻል ሀገራዊ የምግብ ሉአላዊነት ለማረጋገጥ፣ የውጪ ምንዛሬ ለማዳንና የምግብ ዋጋ ንረትን ለመቀነስ ያስችላል። ሆኖም ትኩረት የነበረው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ከምግብ ተመፅዋችነት መላቀቅ ቢሆንም የሀገር ውስጥ የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችል የምርት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛን ተከትሎ በተመረጡ ምርቶች እሴት ሰንሰለትን የተከተለ የአጭርና የረጅም ጊዜ የልማት መርሃ ግብር ለመተግበር የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

- ➔ ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በተመረጡ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ ይነደፋል፣
- ➔ በምርት ማምረት ለሚሳተፉ ተዋንያን የድጋፍና የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የልማት ፕሮግራሞች ይነደፋሉ፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይገነባል።

## 4.5 የገጠር ልማትና መዋቅራዊ ሽግግርን ማረጋገጥ

በሀገራችን የገጠሩ ነዋሪ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዝ ሲሆን የኑሮው መሠረት ግብርና ነው። ይህንን በመገንዘብ መንግስት ግብርናን ማእከል ያደረገ ልማት በማካሄድ፣ ከግብርና ውጪ ያሉ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎችን በማጠናከር እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማትን በማስፋፋት በገጠር የድህነት መጠን እንዲቀንስ ተደርጓል። ሆኖም ግብርና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት አሳክቶ ከግብርናው ዘርፍ የመነጨውን ሃብት ለገጠር ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መፈጠር የሚያስችል ግብርናን ከሌሎች ኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ከማስተሳሰር፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከማስፋት፣ የገጠርና ከተሞች ትስስር ጨምሮ

የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶችን ከማስፋፋት አንጻር አሁንም የሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም።

በተጨማሪም የገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ በተፈለገው ደረጃና ስፋት ለመተግበር የመረጃ ተደራሽ አለመሆን፣ የእውቀትና የአመለካከት ችግሮች፣ የግብርና ሙያ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ በሙያው ለመሰማራት ያለው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ ለወጣቶች እና ሴቶች የሚደረገዉ ድጋፍ ዉስን መሆን፣ የመሬት አቅርቦት፣ የፋይናንስ አቅርቦትና አፈጻጸም ችግሮች፤ የስልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት አለመስፋፋት፣ የገበያ አቅርቦትና ትስስር ማነስ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት፣ የመሠረተ-ልማት በበቂ አለመስፋፋት፣ የአቅም ውስንነት እንዲሁም በግብርና የስራ ዘርፍ ለመስራት የወጣቶች የአመለካከት ችግሮች እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል። ከዚህ አንጻር እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እና የገጠር ነዋሪዎችን ገቢ በማሳደግ የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የገጠር ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት ግብርናን ከሌሎች ኢኮኖሚ ዘርፎች እንዲተሳሰር፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የግብርና መዋቅራዊ ሽግግርን እንዲያግዙ፣ የከተማና ገጠር ትስስር እንዲጠናከር እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ይደረጋል፣ ይህንንም የሚያስተባብር መዋቅር ይሰየማል፣
- የግብርናና የገጠር ልማቱ የገጠር ነዋሪውን ህዝብ የአኗኗርና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥር ይደረጋል፣
- የግብርናና የገጠር ልማቱ ወጣቶችን እና ሴቶችን የሚስብ እና ውጤታማ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ወጣቶች እና ሴቶች በግብርናና ገጠር ልማት ፍትሃዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ለዘርፉ እድገት የላቀ አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ይደረጋል፣
- የግብርና ኢንተርፕረነርሽፕ እና በገጠር ከግብርና ውጭ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ማጎልበቻ የአሰራር ሥርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል።

## 4.6 የግብርና ልማትን ያማከለ የመሠረተ-ልማት ዝርጋታና አቅርቦት

ግብርናን ለማልማት እና የምርት ግብይቱንና እሴት ጭመራ ለማሳለጥ የተቀናጀ የግብርናና ገጠር መሠረተ-ልማት እና አገልግሎት ቁልፍ ሚና አላቸው። የግብርና አገልግሎት መሠረተ-ልማት በተለይም የቴክኖሎጂና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር፣ የእንስሳት እና እፅዋት ጤና አጠባበቅ እና ምርት ጥራት ኳራንታይን መሠረተ-ልማቶች የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት እና ምርት ጥራትና ጤንነት ለመጠበቅ ብሎም የግብርና ምርትና ምርታማነት ለመጨምር፣ የምግብ ደህንነትን ለመጠበቅ

እና የወጪ ንግድ የመዳረሻ ገበያዎች የጥራት ደረጃ አሟልቶ የውጪ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ ወሳኝ ሚና አለው። በመሆኑም መንግስት መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የመንገድና ትራንስፖርት፣ ቴሌኮም አገልግሎት፣ ኤሌክትሪክ፣ የምርት ማቀነባበሪያ (አግሮ ኢንዱስትሪ)፣ የመስኖ አውታሮች እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት ተዘርግቷል። ይህም እስከ አሁን ለተመዘገበው የግብርናና ገጠር ልማት እድገት የበኩሉን አስተዋጽዖ አበርክቷል።

ሆኖም የመሠረተ-ልማት ዝርጋታዎች የግብርና የመልማት አቅም ግምት ውስጥ በበቂ ሁኔታ ያላስገቡ፣ የተገነቡትም ቢሆን በበቂ መጠንና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ አለመስፋፋት፣ የመሠረተ-ልማቶቹ አገልግሎት አቅርቦት የተገልጋዮቹን ፍልጎት እና አለም አቀፍ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ የሚያስችል የተሟላ የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም። በተለይም የማቀዝቀዣ ሰንሰለት ፣ ዘመናዊ የእንስሳት ማጓጓዣ እጥረት እና ለመሠረተ-ልማት ግንባታ በቂ የብድር አገልግሎት አለመኖር፣ ማከማቻ፣ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቱ የተሟላ መጋዘኖች በበቂ ደረጃ አለመኖር እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት አለመዘርጋት በአምራቾች፣ በተጠቃሚው እና በሀገራዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል።

የፌዴራልና እና የክልል የእፅዋትና እንስሳት ኳራንቲን ላቦራቶሪዎች፣ መግቢያና መውጫ ኬላዎች በሚፈለገው መጠን አልተዘረጉም። ከዚህም በተጨማሪ የተሟላ የድህረ-መግባት ኳራንቲን እና በመስክ ማቆያ ቦታዎችና ማስወገጃ ፋሲሊቲ፣ እንዲሁም ገቢና ወጪ እፅዋትና የእፅዋት ውጤቶች ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ አፍላቶክሲንና ሌሎች ባዕድ ነገሮች ነጻ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት አልተዘረጋም። የፀረ-ተባይ አስተዳደር፣ አጠቃቀም፣ ደህንነት ጥበቃ እና ስርጭት ቁጥጥር የሚያገለግሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኖችና መርጫ መሳሪያዎች፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለማስወገድ የሚያስፈልጉ መሠረተ-ልማቶች በሚፈለገው ጥራትና ብዛት አልተዘረጉም። የርጭት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የአውሮፕላን ማኮብኮቢያ ሜዳዎች በበቂ ሁኔታ አልተሟሉም። በተመሳሳይም የአፈር ማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር መሠረተ-ልማት ባለመዘርጋቱ አዲስ ማዳበሪያ ለማስመዝገብና ጥቅም ላይ ለማዋል አልተቻለም።

በሌላ በኩል የቁም እንስሳት ገቢና የወጪ ንግድ ለቁጥጥር የሚያስፈልጉ የኳራንቲን መሠረተ-ልማት በበቂ መጠን ባለመዘርጋታቸው እና ያሉትም የአገልግሎት ጥራት መጓደል ምክንያት በመዳረሻ ገበያ የምርት ጥራትና ደህንነት ተቀባይነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል። በተጨማሪም ለእንስሳት ውጤቶች የጥራት ማረጋገጫ ለመስጠት ዕውቅና የተሰጠው ላብራቶሪ በሀገር ውስጥ ባለመኖሩ ምክንያት በውጪ ምንዛሬ ከሀገር ውጪ እንዲመረመር መደረጉ የተጠናከረ የእንስሳት የኳራንቲን አገልግሎት ለመስጠት አዳጋች ሆኗል። የወጪ ንግድ መዳረሻቸውን መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የሆኑ ቁም እንስሳት በትራንዚት ሀገር ማረፊያ ቦታ ባለመዘጋጀቱ ምክንያት ድጋሚ

ሰርተፍኬት ተሰጥቷቸው እንዲላኩ መገደድ ላኪዎችን ለእንግልት እና ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉ ባሻገር በሶስተኛ ሀገር ስም ኤክስፖርት እንዲደረግ አስገድዷል። ይህም ሀገራችን ማግኘት የሚገባትን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ገቢ አሳጥቷታል። የእንስሳት ቄራዎች አገልግሎት በተገቢው መስፈርትና ደረጃ ባለመገንባታቸው አገልግሎቱ የተደራሽነትና ጥራት ጉድለት ከማስከተሉም በላይ የህገወጥ እርድ እንዲስፋፋ አድርጓል። በሌላ መልኩ ፍላጎት ያላቸው የግል አገልግሎት አቅራቢዎች ወደ ስራ ለመሰማራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በተለይም የከተማ ማስተር ፕላን ሲዘጋጅ ለቄራ አገልግሎቶች የሚሆን ቦታ ባለመለየቱ አገልግሎቱ በመንግስት እንዲወሰን አድርጎታል። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

- ➔ የግብርናና ገጠር መሠረተ-ልማት (የመንገድና ትራንስፖርት፣ ቴሌኮም አገልግሎት፣ የኃይል፣ ምርት መሰብሰቢያ መጋዘን፣ የምርት ማቀነባበሪያ (አግሮ ኢንዱስትሪ)፣ የመስኖ አውታሮች፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት፣ ደረጃውን የጠበቀ የገጠር መኖሪያ ቤቶች፤ ውኃ አቅርቦት፣ የእርሻ ውስጥ መንገዶች፣ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ በተሻለ ሁኔታ እንዲደገፍ የልማት አካባቢዎች የግብርና የመልማት አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ይገነባል፣
- ➔ የተቀናጀ መሠረተ-ልማት ለማስፋፋት የመንግስት እና የግል ዘርፍ አጋርነት ይጠናከራል፣ የግሉ ዘርፍና የህብረት ስራ ማህበራት ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- ➔ የከተማና ገጠር ትስስር ይጠናከራል፣ የተቀናጀ የገጠር አገልግሎቶች እንዲስፋፋ ይደረጋል፣
- ➔ የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት እና ምርት ጥራትና ደህንነት በተሟላ መልኩ ለማስጠበቅ የእንስሳት እና እፅዋት ጤና አጠባበቅ፣ የጥራትና ኳራንቲን አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰከረላቸው (Accredited) እንዲሆኑ እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አሰራር እንዲቀናጁ ይደረጋል፣
- ➔ የአገልግሎት መሠረተ-ልማቶች በመንግስትና የግል ዘርፉ አጋርነት እንዲገነቡና እንዲተዳደሩ ይደረጋል፣
- ➔ የግሉ ዘርፍ በአገልግሎት መሠረተ-ልማት ዝርጋታና አስተዳደር ጉልህ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል።

## 4.7 ቢዝነስና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት

የግብርና ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የተሻገረ ግብርና እውን ለማድረግ ቢዝነስና ኢንቨስትመንት በግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት በማቅረብ፣ ምርት ማምረት፣ ግብይትና እሴት ጭመራ አገልግሎቶች በውጤታማ መልኩ ማስፋፋት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የግብርናን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ

ዘርፎች ጋር ለማስተሳሰርና የገጠር መዋቅራዊ ሽግግሩን ለማሳካት ወሳኝ ሚና አለው። በመሆኑም ለሀገራችን ግብርና መሠረት የሆነውን ባለ አነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር እና አርብቶ አደር ወደ ቢዝነስና ኢንቨስትመት ማሻገር፣ የህብረት ስራ ማህበራትን ማጠናከር እና የግል ዘርፉን ካፒታል ኢንቨስትመንት ማስፋፋት የፖሊሲ አቅጣጫ ትኩረት ሆነው ይተገበራሉ።

### 4.7.1 የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች እና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና ስርጭት፣ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ንግድ ምርቶች ግብይት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት፣ የቁጠባና ብድር አገልግሎቶችን ማቅረብ ለግብርናው ልማትና ግብይት ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም አርሶና አርብቶ አደሮችን በማደራጀት ምርቶቻቸውን በማሰባሰብና በማከማቸት የመጋዘን አገልግሎት እንዲሁም የምርት ደረጃ የመለየትና የማሸግ አገልግሎት በመስጠት ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ፣ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትን በማሳጣር የተሻለ ዋጋ እንዲያገኙና ኑሮአቸው እንዲሻሻል ማድረግ ነው።

ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደር ሥርዓት ማህበራቱን በነፃ ገበያ ሥርዓት ውስጥ ለመወዳደር የሚያስችል፣ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት እና ኢንቨስትመንትን የሚያመቻች አልነበረም። በተጨማሪም የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን፣ የብቃት ደረጃ እና የእውቅና አሰጣጥ በተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እና አሰራር ሥርዓት አልተደገፈም። የኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶች የግብይት ድርሻ አነስተኛ መሆኑ፣ በወጪ ንግድ ላይ ያላቸው ድርሻ በመጠን ውስን መሆኑ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን እና የፍጆታ ምርቶችን ከውጪ በጅምላ ለማስገባት በቂ አቅም አለመፍጠራቸው በዘርፉ ላይ ያላቸው ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉን ያመላክታል።

የኅብረት ሥራ ማህበራት በተሳተፉባቸው የግብርና እና የፍጆታ ምርቶች አቅርቦት ላይ የመጠን፣ የጥራት እና የወቅታዊነት ጉድለቶች ታይቶባቸዋል። ለዚህም በዋናነት የተለዩ ምክንያቶች ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እና መሠረተ-ልማት አለመዘርጋት ናቸው። የኅብረት ሥራ ማህበራትን አዋጭነት ባለው መልኩ፣ ያለ በቂ ግንዛቤና ፈቃደኝነት አለመደራጀት፣ የአደረጃጀትና አመዘጋገብ ሥርዓት ወጥ አለመሆን እና ጠንካራ አደረጃጀት አለመኖሩ ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። ስለሆነም የህብረት ስራ ማህበራትን ውጤታማ ለማድረግ የሚከተሉት አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

- ➔ የኅብረት ሥራ ማህበራት ገለልተኛነታቸውን ከሚጻረር የውጭ አካል ተጽዕኖ ተላቅቀው በገበያ ሥርዓት ውስጥ ይበልጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

- ➔ የአመራር፣ ቁጥጥርና ቅጥር ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት በለየ ሁኔታ አስተዳደራቸው በቅጥር ባለሙያዎች እንዲመራ ይደረጋል፣
- ➔ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ይበልጥ ተወዳዳሪ ለማድረግ የማዋሃድ ወይም የመሰብሰብ አማራጭን እንዲከተሉ ይደረጋል፣
- ➔ የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ግብዓት አቅርቦትና ግብይት፣ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች፣ ምርት ገበያ፣ እሴት ጭመራ፣ ብድርና ቁጠባ እና መሠረተ ልማት አቅርቦት በስፋት፣ በጥራትና ተወዳዳሪነት ባለው መልኩ እንዲያቀርቡ ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል፣
- ➔ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንቨስትመንትን ለማስፋት የሚያስችል አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን እንዲጠቀሙ ይደረጋል፣
- ➔ የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን እና የብቃት እውቅና ደረጃ አሰጣጥ ይጠናከራል።

### 4.7.2 የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማጠናከር

የግሉ ዘርፍ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎትን በማቅረብ፣ በቀጥታ ምርት ማምረት፣ ግብይትና እሴት ጭመራ አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ ለግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ያለው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። የግሉ ዘርፍ በግብርና ልማትና ግብይት ውስጥ ያለው ተሳትፎና ውጤታማነት ከፍተኛ ፋይዳ ቢኖረውም ከአገልግሎትና ሌሎች ዘርፎች ጋር ሲነፃፀር የግብርና ልማት ከፍተኛ ልፋት የሚጠይቅ፣ ለከፍተኛ ሥጋት (risk) የተጋለጠ በመሆኑ፣ የትርፍ ህዳጉ ዝቅተኛ ስለሆነ የግሉን ዘርፍ በግብርና ልማት ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ ለማሳተፍ እና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ያገናዘበ የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም። በተጨማሪም በማደግ ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮችን በመደገፍና በማበረታታት ወደ ኢንቨስትመንት ለማሻገር የሚያስችል በቂ ትኩረትና የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም።

በሌላ በኩል የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት የሚመራበት የተሟላ የአሰራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ አርሶና አርብቶ አደሩን የማፈናቀል አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል። ይህም የአካባቢው ነዋሪዎች ልማቱን በበጎ እንዳያዩት ከማድረጉ በተጨማሪ ለልማቱ የደህንነት ስጋት ሆኖ ቆይቷል። በሌላ መልኩ በዘርፉ የሚሰማሩ ተዋንያን የሚለዩባቸው መስፈርቶች ባለመቀመጣቸው ለልማቱ አወንታዊ ሚና የማይጫወቱ ተሳታፊዎች ይዞ መቀጠሉ ውጤታማነቱን ተፈታትኖታል። በተጨማሪም የብድር እና ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ድጋፍ የተሰጣቸው ባለ ሃብቶች ከታለመለት የግብርና ልማት ውጭ ለሌላ ዓላማ እያዋሉ ይገኛሉ።

የውጪ ኩባንያዎች መዋዕለ ንዋያቸውን በግብርና ላይ አፍስሰው የሚያገኙትን ትርፍ ወደ ዋና መስሪያ ቤታቸው ልከው ለባለ አክሲዮኖች ለማከፋፈል በሀገራችን ባለው የውጪ ምንዛሬ እጥረት የተነሳ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም። ይህም የውጪ

ኩባንያዎች በሀገራችን ግብርና እንዳይሰማሩ ወይም ያሉትም ኢንቨስትመንቶች እንዳያስፋፉ እንቅፋት ሆኖ ይገኛል።

ጉምሩክ የሚቆጣጠረው የገቢ ካፒታል ዕቃዎች አሰራር በተመዘገቡ ዝርዝር ብቻ በመሆኑ አዳዲስ በዝርዝሩ ያልተካተቱ የግብርና ቴክኖሎጂና መሣሪያዎችን ለማስተናገድ አያስችልም፤ ይህም ክልከላ በየጊዜው የሚወጡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለግብርና ዘርፍ እድገት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ የግል ዘርፍ ተዋንያንን ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት ዳርጓቸዋል።

የመንግስትና የግል አጋርነት የህግ ማዕቀፍ ዝቅተኛ የካፒታል መነሻ መጠኑ የግብርና ዘርፍ መሠረተ-ልማቶች ለማሟላት አዳጋች መሆኑና መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በፌዴራል ደረጃ ላይ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ በዘርፉ የመንግስትና የግል አጋርነትን ለመተግበር እንዳይቻል አድርጎታል። የሰው ኃይል ልማት ፍላጎት ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር ባለመተሳሰሩ የግሉ ዘርፍ የሚያስፈለገውን ብቃት ሊያሟላ አልቻለም። በመሆኑም የግሉ ዘርፍ ውጤታማነትና ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከመፍጠሩም በላይ ስራ ፈጣሪ ምሩቃንን በሚጠበቀው ደረጃ ማፍራት አልተቻለም። ስለዚህ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ➔ አቅም በመፍጠር ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን ወደ መካከለኛ ግብርና አልሚነት እንዲሸጋገሩ የሚያስችል ድጋፍና ማበረታቻ ይሰጣል፣ በተጨማሪም የዘርፉን ባለሙያዎች ድጋፍና ማበረታቻ በመስጠት በግብርና ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ይደረጋል፣
- ➔ የሰፋፊ ግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ይደረጋል፤ እንዲሁም የኢንቨስትመንት፣ ንግድ፣ ታክስ እና ጉምሩክ የህግ ማዕቀፎች (የማበረታቻ ሥርዓት፣ የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ብቃት ማረጋገጫን ጨምሮ) የግብርናን ልዩ ባህሪ ባገናዘበ ሁኔታ ልማቱንና ግብይቱን እንዲደግፉ ይደረጋል፣ ውጤታማነቻው ይረጋገጣል፤
- ➔ የመንግስትና የግል አጋርነት የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር ሥርዓት የግብርና ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ ልማቱን እንዲደግፍ ይደረጋል።

## 4.8 የግብርናና ገጠር ልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነት

ፋይናንስ የግብርናን ምርት፣ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ወሳኝ መሳሪያ ነው። የገጠርና የግብርና ፋይናንስ ሥርዓቱም በዋናነት በገጠር የሚገኙ የባንክ ቅርንጫፎች የሚያቀርቡትን የብድር መጠን ከፍ በማድረግ ከቡድን ብድር በተጨማሪ የአርሶና አርብቶ አደሩን ምርት እንደ ዋስትና በማስያዝ የግል ብድር መውሰድ እንዲሁም ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር ትስስር በመፍጠር ተደራሽነታቸውን እንደሚጨምሩ አቅጣጫ ተቀምጦ ነበር። እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሌሎች የፋይናንስ ተቋማትን ከግብርና ጋር በማስተሳሰርም ሆነ የራሳቸውን ባንክ

በማቋቋም የገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ግንባታን እንዲያግዙ በፖሊሲ አቅጣጫው ከመጠቆሙም ባሻገር ሌሎች የፋይናንስ አማራጮችን ለማስፋፋት የአሰራር ሥርዓት እንደሚያስፈልግ ተመላክቷል።

ሆኖም የመደበኛ ባንኮችና መድን ድርጅቶች ግብርናን በተለይም አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮችን እና አርብቶ አደሮችን በተገቢው ለማገልገል የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ እንዲሁም የፖሊሲ ባንክ የሆነው የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ቢሆን ትኩረቱ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመሆኑ ለዘርፉ የቀረበው የፋይናንስ አገልግሎት አነስተኛ ነው። አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ለግብርናና ገጠር ምቹ የሆነ የቡድን ዋስትና የመሳሰሉ አሰራሮች ቢኖሯቸውም ያላቸው የካፒታል አቅርቦት ከፍላጎት አኳያ ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚጠበቀውን ያህል የፋይናንስ አገልግሎት ማቅረብ አልቻሉም። እንዲሁም ሌሎች የፋይናንስ አማራጮችን ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም።

በዚህም የተነሳ በአሁኑ ወቅት ከባንኮች ከሚቀርበው አጠቃላይ ብድር ውስጥ የዘርፉ ድርሻ ዝቅተኛ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር እና አርብቶ አደሩ የቀረበው ውስን ነው። በሌላ መልኩ በፋይናንስ ተቋሟት የሚጠየቀው ከፍተኛ የብድር ዋስትና ጥያቄ እና የወለድ ምጣኔ ከብድር ፈላጊው ህብረተሰብ አቅም ጋር ያልተገናዘበ ነው። ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ ተዘዋዋሪ የብድር ሥርዓት ቢዘረጋም የብድር ተመላሽ መጠን ዝቅተኛ በመሆኑ የብድር ሥርዓቱን በዘላቂነት ለማስቀጠል ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል።

የመድን አቅርቦትም በአብዛኛው በአጠቃላይ የመድን አገልግሎት ላይ ያተኮረ ነው። በፕሮጀክት ደረጃ ከተተገበሩ ውስን የግብርና መድን ሽፋን አይነቶች ልምድ ወስዶ በማስፋት የተጠናከረ የግብርና መድን ሽፋን በሀገር ደረጃ አልተስፋፋም። ከውጪ የሚመጡ የአክስዮን ካፒታል ግብርና ላይ አዋጭ በሆነ መልኩ ሃብታቸውን የሚያፈሱበት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ካፒታላቸውን ከግብርና ውጪ ባሉ ሌሎች ዘርፎች ላይ እንዲያፈሱ ተገደዋል። የህብረት ሥራ ማህበራት የመሠረተ-ልማት ፍላጎት በፕሮጀክት ፋይናንስ አሰራር እንዲገነባ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ በመንግሥት ውስን በጀት ላይ ብቻ እንዲወሰኑ አድርጎታል። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

- ➔ የግብርናና ገጠር ልማት የብድር አቅርቦት ለማሻሻል ባንኮች ዘርፉ ካለው ሁለንተናዊ አስተዋጽዖ አንፃር የሚያበረታታ የብድር ድርሻው (loan portfolio) እንዲያድግ ይደረጋል፣ ይህንኑ የሚያስተባብር ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል፣
- ➔ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በተለይም የመሬት የመጠቀም መብት፣ እንስሳት፣ ግብርና ምርቶች፣ እንዲሁም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችንና ቋሚ ተክሎች ለብድር ማስያዣነት መጠቀም ይፈቀዳል፣

- ➔ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፣
- ➔ የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት አሰራር የዘርፉን ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ እንዲቀርብ ይደረጋል፣
- ➔ የግብርናና ገጠር ልማት መድን ሽፋን ለማሻሻል መደበኛ ኢንሹራንስ ድርጅቶች የዘርፉን የአደጋ ተጋላጭነት እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚካለው አስተዋጽዖ አንፃር የሚያበረታታ የመድን ድርሻው (insurance portfolio) እንዲያድግ ይደረጋል።

## 4.9 የዘርፉን የማስፈጸም አቅም መገንባት

የዘርፉን የማስፈጸም አቅም ለመገንባት የሰው ኃይል ልማት፣ የተቋማት ትብብርና ተጠያቂነት ሥርዓት ዝርጋታ፣ የትምህርትና ስልጠና እና የግብርና ዘርፍ ተቋማት ትስስርና ተጠያቂነት ሥርዓት የዲጂታል ግብርና እና ኮሙኒኬሽን የአሰራር ሥርዓት የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.9.1 የሰው ኃይል ልማት

የሰው ኃይል በብቃት፣ በቅልጥፍናና በውጤታማነት በማደራጀት እና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የተገልጋዮች እና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማርካት ወሳኝ ነው። ይህንኑ መሠረት በማድረግ መንግስት የሙያና የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በተለይም የሰው ሃብት ሥራ አመራር ሥርዓት ስራ ላይ በማዋል በሀገሪቱ ለተመዘገበው እድገት የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል።

ሆኖም የነበረው የትኩረት አቅጣጫ በአመዛኙ የቀበሌ ልማት ባለሙያዎች ላይ ሲሆን በዘርፉ ውስጥ ስለአሉት ሌሎች ባለሙያዎች ውጤታማነትና ተጠያቂነት እንዲሁም የማትጊያ እና የደረጃ እድገት ሥርዓት በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም። በተጨማሪም ዘርፉ በሙያው በሰለጠነ የሰው ኃይል የሚመራበት አሰራር አልተፈጠረም። የአመራሩ የብቃት መገምገሚያ ሥርዓት ያልተቀመጠለት ከመሆኑም ባሻገር ኃላፊነትና ተጠያቂነት ስለሌለው ድክመትን አርሞ ሥራውን ለማቀላጠፍ አልተቻለም። ሌሎች የማበረታቻ፣ ተሳትፎ፣ የሰው ሃብት ሙሌት፣ የሰው ሀብቱ የስራ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ዝርጋታ፣ ስልጠና መስጠት፣ የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት፣ የፕሮግራም ቀረፃ፣ የትግበራ እና የውጤታማነት ግምገማ፣ ስልታዊ የተተኪ አመራር ማዘጋጀት እና የእውቀት ስራ አመራር ሥርዓት ሳይዘረጋ ቆይቷል። ምቹ የስራ አካባቢ ደህንነት እና ጤንነት የሚያረጋገጥ የአሰራር ሥርዓት ባለመኖሩ ሠራተኞችን ለሥራ የሚያነሳሳ የስራ ስምሪትና አሰራር ለመዘርጋት ባለመቻሉ ብቃት ያላቸውን ሠራተኞች ለማቆየትም ሆነ አዳዲስ ሠራተኞችን ለመሳብ አዳጋች ሆኗል። በመሆኑም በቀጣይ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ➔ ባለሙያና አመራር ለማደራጀት ዕውቀትን፣ ክህሎትንና ብቃትን መሠረት ያደረገ የምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ ሥርዓት ለመዘርጋት ኃላፊነትና ተጠያቂነት፣ እንዲሁም ዘርፉ ሳቢ እና ምቹ የስራ አካባቢ፣ ደህንነትና ጤንነት ሥርዓት የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ ይደራጃል፣ በቀጣይም የማብቃት ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ➔ የአርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደርና አርብቶ አደርን አቅም በየደረጃው ለመገንባት እና አስፈላጊ እገዛ ለማቅረብ ብቃታቸው የሚመዘንበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

### 4.9.2 የተቋማት ትብብርና ተጠያቂነት ሥርዓት

ግብርና በባህሪው ረጅም የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ የብዙ ተቋማት ተሳትፎና ድጋፍ እንዲሁም ቅንጅትና ትብብርን ይፈልጋል፡፡ የተቋማት የስልጣን ወሰን በማይነካ ሁኔታ ለመተግበርና ለማስተግበር ትብብርና ተጠያቂነት በሰፈነበት አኳኋን ማከናወን ግቦቻችንን ለማሳካት አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ ትብብር እንዲፈጠር ማድረጉ በሀገራዊ የግብርና ልማት ርዕይና ዓላማዎች ላይ የጋራ መግባባት ለመያዝ፣ ሀገራዊ የግብርና ልማት ፕሮግራሞችን ከአዳጊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እና ከአባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም፣ የግብርናውን ዘርፍ ተመጋጋቢነትና ትስስር ለማጎልበትና በተነፃፃሪ ዕድሎች ላይ የተመሰረተ ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ፣ ሃብትን በቅንጅትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ይረዳል፡፡ በግብርና ዘርፍ አደረጃጀቶች እና በግብርና ልማት ላይ ወሳኝ ድርሻ ያላቸው አካላት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው ከግል ተቋማትና የልማት አጋር አካላት ጋር የትብብርና ተጠያቂነት አሰራር ሥርዓት መዘርጋት ዘርፉን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ከዚህ አንጻር በቀጣይ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ፡፡

- ➔ በፌዴራል እና በክልል የተዘረጉ የግብርና ዘርፍ ፈፃሚዎች ሚናቸውና ኃላፊነታቸው ተለይቶ ተጠያቂነት የሰፈነበት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- ➔ የግብርና ተቋማት ከሌሎች ዘርፎች ተቋማት እንዲሁም ዘርፉን ከሚደግፉ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማት ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- ➔ የተቋማት የጋራ ዕቅድ ክትትልና ግምገማ እና የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ይጠናከራል፡፡

### 4.9.3 የትምህርት፣ ስልጠና እና የግብርና ዘርፍ ተቋማት ትስስር ሥርዓት

የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በፍጥነት በመስፋፋት ለዘርፉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ተቋማት ትስስርና ውጤታማ በሆነ መንገድ ዘርፉ የሚያስፈልገውን

የሰው ኃይል ማፍራት አልቻሉም። በተለይም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በአብዛኛው ለመንግስት ቅጥር የሚያሰለጥኑ በመሆኑ ለግሉ ዘርፍ የሚያስፈልግ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት አልተቻለም። በመሆኑም በቀጣይ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ➔ የግብርና ልማት፣ ምርምር እና ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ትስስርና ተጠያቂነት የሰፈነበት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸውይደረጋል፣
- ➔ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርትና ስልጠና በግብርና ዘርፍ የሰው ኃይልና ክህሎት ፍላጎት መሠረት እንዲመራ ይደረጋል።

### 4.9.4 የዲጂታል ግብርና የአሰራር ሥርዓት

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በተለያዩ ዘርፎች የለውጥ መሳሪያ በመሆን ሀገራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግና የማህበረሰብን ተጠቃሚነት ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያበረከተ ይገኛል። በግብርናው መስክ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ምርታማነትንና በገበያ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ወቅታዊ መረጃን መሠረት በማድረግ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና ምክረ-ሐሳቦችን በሚፈለገው ቦታ ለመስጠት፣ ለትክክለኛነት የቀረበ የግብርና ሜካናይዜሽን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ፣ ዲጂታል ኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ፣ የግብርና ግብአትና ምርት ዱካ ለመከታተል፣ የሰብልና እንስሳት ተባይና በሽታ ቅኝትና የሥጋት ትንተና ለማድረግ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት፣ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ አገልግሎት ምቹ ለማድረግ፣ የግብርና ምርት ትንበያ ለመስጠት፣ የግብርና ግብይት፣ የግብርና መረጃ በየፈርጁ በማደራጀት ለፖሊሲ አውጭዎችና ውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲሁም ለተጠቃሚው በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ፣ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ አሰጣጥ ሥርዓትን በየደረጃው ለመዘርጋት፣ የጂኦ-ስፖሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተጎሳቆሉ፣ ያገገሙ፣ የለሙ መሬቶችን በቀላሉ ለመለየት እና የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም መረጃ ለመዘርጋት ያስፈልጋል።

ይሁን እንጂ የመረጃ አሰባሰብ ወጥ አሰራር ባለመኖሩ መረጃዎች እርስ በእርስ የሚጣጣሙ ያለመሆን፣ በግብርና ውስጥ የበለጸጉ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (የኢኮቴ) የተበጣጠሱና እርስ በእርስ የማይመጋገቡ መሆን፣ የግብርና መረጃ አያያዝና ልውውጥ አሰራር ያለመኖር፣ ኢኮቴ ልማትና ኢንቨስትመንት በዘላቂነት በፕሮግራም ያለመመራት፣ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መሠረተ-ልማት በሚፈለገው ልክ አለመዘርጋት፣ የኃይል አቅርቦትና የኢንተርኔት አገልግሎት በተለይም በገጠራማ አካባቢ አለመኖር፣ የበለጸጉ የኢኮቴ መረጃ ሥርዓቶችን የመጠቀም አቅም እንዲሁም ፈቃደኝነት ማነስ፣ በኢኮቴ የተሰማሩ የግል ዘርፎች በግብርናው መረጃ ሥርዓት ማዘመን ዙሪያ አስተዋጽዖ ማነስ የሚጠቀሱ ናቸው። ግብርናን በኢኮቴ ለመደገፍ የተለያዩ ስራዎች የተሞከሩ ቢሆንም አብዛኛዎቹ በሙከራ ላይ

ተገድበው በመቅረታቸው፣ የተበጣጠሱና እርስ በእርስ የማይመጋገቡ በመሆናቸው የሥራ ድግግሞሽና የሃብት ብክነት መኖሩ እንዲሁም በግብርናው ዘርፍ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እጅግ አነስተኛ መሆኑ በግብርናው ዘርፍ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም። በመሆኑም በቀጣይ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ➔ የግብርናው ዘርፍ የዲጂታል አሰራርን የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ➔ የተቀናጀ የግብርና የዲጂታላይዜሽን ስትራቴጂ፣ የዲጂታል መሠረተ-ልማት፣ የሰው ኃይል፣ የግብርና መረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምና የልውውጥ አቅም የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል።

### 4.9.5 ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት፣ አገልግሎት፣ ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር

የሰብል ቴክኖሎጂና ግብዓት ምዝገባ እና ቁጥጥር ስራ በተጠናከረ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር ባለመስፈኑ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት የሌለባቸው (ያልተመዘገቡ እና የተከለከሉ) ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንዲሁም በህገ ወጥ ንግድ የሚዘዋወሩ ኬሚካሎች እንዲበራከቱ መሆኑና ይህም ለሰብል ምርት መቀነስ፣ ጥራት ጉድለትና መባከን ከማስከተሉም በላይ በምግብና በሰው ጤንነትና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል። በተጨማሪም ገለልተኛ የቴክኖሎጂ ለቀቃና ምዝገባ የተጠናከረ ባለመሆኑ የምርታማነታቸውና በሽታ ከመቋቋም አቅማቸው አንፃር የተሻሉ የማይባሉ የሰብል ዝርያዎች እየተለቀቁ መሆኑ እንዲሁም ለሀገራችን ተስማሚነታቸው ያልተረጋገጡ ዝርያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በር ከፍቷል።

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ በብሔራዊ ደረጃ በመወሰኑ እና በክልልና ታች ባሉ የግብይት ሰንሰለት፣ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የቁጥጥር መዋቅሩ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ጥራታቸውን ያልጠበቁ መኖ እና ፈዋሽነታቸው ያልተረጋገጡ መድሃኒቶች ወደ ተጠቃሚው እንዲደርስ ብሎም የህገወጥ የሀገር ውስጥ እና ድንበር ዘለል ንግድ በመስፋፋቱ የእንስሳት ምርታማነትን እየጎዳ ይገኛል።

በብዙ ተዋንያን የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች እና ሁሉንም የሚቀርቡ ግብዓቶች እና የሚሰጡ አገልግሎቶች ቁጥጥር ሥርዓት፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለቤትነት መብት ጥበቃ እና ሮያሊቲ ክፍያ ሥርዓት፣ የግል ዘርፍ እንዲሁም ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደርና እና አርብቶ አደሮች የሚሰጡ ማበረታቻዎችን አፈጻጸም ክትትል ሥርዓት አልተዘረጋም። እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ➔ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት፣ አገልግሎት እና ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ጠንካራና ከአስፈፃሚ ተቋማት ተፅዕኖ በተላቀቀና የጥቅም ግጭት እንዳይኖረው ሆኖ እንዲዋቀርና እንዲጠናከር ይደረጋል፣

- ➔ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት፣ አገልግሎት እና ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ሥርዓት፣ ተቋማዊ አደረጃጀት እና መሠረተ-ልማት ይዘረጋል።

## 4.10 የግብርና አካታችነትና ዘላቂነት ማሳደግ

ዘላቂና አካታች የግብርና ልማትን እውን ለማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ግብርና ልማት ማካሄድ፣ የተፈጥሮና ብዝሃ-ሕይወት ሃብት አጠቃቀምን ማሻሻል፣ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ እንዲሁም ትኩረት ያጡ የማህበረሰብ ክፍሎችን በልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል። የመልማት እምቅ አቅማቸውን አሟጠው ያልተጠቀሙ እንደ አርብቶ አደር እና የምግብ ዋስትናን ያላረጋገጡ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት ይፈልጋሉ። በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ ዋነኛ የምግብ ምንጭ ስለሆነ በንጥረ-ምግብ ይዘቱ የበለጸገ የምግብ አቅርቦትና ተደራሽነት ማረጋገጥ ይፈልጋል። ከዚህ አንጻር ከላይ በተዘረዘሩት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተካተው ከሚተገበሩት በተጨማሪ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል።

### 4.10.1 የአየር ንብረት ለውጥን ያገናዘበ የግብርና ልማት

- ➔ የመሬትና ተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ የቴክኖሎጂ ማፍለቅና ማስረፅ፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የፋይናንስ አገልግሎት፣ የሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲሁም የተቀናጀ መሠረተ-ልማት ማስፋፊያ (መስኖ ልማትን ጨምሮ) ስራዎች እየተለዋወጠ የመጣውን የአየር ጸባይ በሚመልስ መልኩ በመተግበር ከአየር ንብረት ለውጥ እና ከተፈጥሮ ጋር የተሳሰረ ግብርና ልማት ይተገበራል፣
- ➔ የግብርና ምርትና ምርታማነት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ የአካባቢ፣ የተፈጥሮና ብዝሀ ሕይወት ሃብት እንክብካቤና አጠቃቀም ውጤታማነትን ለመጨመር፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአካባቢ ሚዛንን ለማስጠበቅ እና በየጊዜው የሚከሰቱ የተፈጥሮ መዛባት መስተጋብር የሚፈጥር ግብርና ልማት እንዲተገበር ይደረጋል።

### 4.10.2 የምግብ ዋስትና እና አደጋን የመቋቋም አቅም ማጠናከር

- ➔ ስር ለሰደደ የምግብ ዋስትና አለመረጋጋጥ እና በተለያዩ ጊዜያት በሚከሰቱ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ውጤታማ ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል። የአደጋ ስጋት የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ ምላሽ እና የመልሶ ማቋቋም አቅም እና ሥርዓት ይጠናከራል።

### 4.10.3 የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት

➔ የሴቶች በግብርና ልማት ውጤታማ ተሳትፎና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ለዘርፉ እድገት የላቀ አስተዋጽዖ ማበርከት እንዲችሉ የመሬት የመጠቀም መብት፣ የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት፣ ቴክኖሎጂና ግብዓት፣ ፋይናንስ አገልግሎት፣ የገበያ ትስስርና እሴት ጭመራ አገልግሎት፣ አቅርቦትና ተደራሽነት እንዲሁም ከግብርና ውጪ ባሉ የገጠር ኢኮኖሚ ልማት ተሳትፏቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል ።

### 4.10.4 የአካል ጉዳተኞችና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት

➔ የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ ምክንያቶች ከህብረተሰብ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በግብርና ልማት ውጤታማ ተሳትፎና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ለዘርፉ እድገት የላቀ አስተዋጽዖ ማበርከት እንዲችሉ የመሬት የመጠቀም መብት፣ የኤክስቴንሽን ምክርና አገልግሎት፣ ቴክኖሎጂና ግብዓት እና ፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦትና ተደራሽነት እንዲሁም ከግብርና ውጪ ባሉ የገጠር ኢኮኖሚ ልማት ተሳትፏቸው ይረጋገጣል። በተጨማሪም የአረጋዊያን አርሶና አርብቶ አደሮች የምግብ ዋስትናና አደጋን የመቋቋም አቅም እንዲያጠናክር ድጋፍ ይደረጋል።

### 4.10.5 ዘላቂ የአርብቶ አደር አካባቢ ግብርና ልማት

➔ የቆላማ አካባቢ ግብርና ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ የአካባቢውን ሥርዓተ-ምህዳርንና የአኗኗር ዘይቤን ባገናዘበ መልኩ እንዲስፋፋ ይደረጋል፣

➔ በገበያ የሚመራ እንስሳት ሃብት ልማት፣ ውሃን ማእከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት፣ የመሬትና ተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የተቀናጀ የግብርና ምርምርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ማጠናከር ላይ በትኩረት ይሠራሉ፣

➔ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር እንዲተሳሰር ይደረጋል፤ አማራጭ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፋ ይደረጋል፣

➔ የአርብቶ አደር አካባቢ የከተማና ገጠር እና ከሌሎች ሥርዓተ-ምህዳሮች ጋር ትስስር ይጠናከራል፤ የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች እንዲስፋፋ ይደረጋል።

### 4.10.6 የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና ሥርዓት

➔ ለዜጎች በቂ፣ የተሰባጠረ፣ በንጥረ-ምግብ ይዘቱ የበለፀገና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትና አጠቃቀም በዘላቂነት

ለማሻሻል የሥርዓተ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን ይተገበራል፣

➔ በምግብ ንጥረ-ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ፣ ዋጋቸውም ተመጣጣኝ እንዲሆን፣ የምርቶቹን የምግብና የንጥረ-ነገር ብክነትን ለመቀነስ፣ የምርቶችን ጥራትና ደህንነት ለመጠበቅ እና የተሰባጠረ የአመጋገብ ባህልን ለማስረፅ በትኩረት ይሰራል።

## 5 . የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች

**ዘላቂ ምርትና ምርታማነት እድገት፦** የተሻሻለ የመሬት ደንና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር በማስፈን፣ የምርት ሥርዓት በማጎልበት፣ የግብዓት እና የአገልግሎት አሰጣጥን በማጎልበት እና በማሳለጥ፣ የግብርና ውሃ አጠቃቀምን በማሻሻል እንዲሁም የግብርና ዘርፍን የማስፈጸም አቅም በማጎልበት የግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው መልክ እንዲያድግ ይደረጋል።

**ያደገ የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን (ለወጪ ንግድ ፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ እና የሀገር ውስጥ ገበያ አቅርቦት እንዲሁም ገቢ ምርት መተካት)፦** የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች የሰብልና ሆርቲካልቸር፣ እንስሳትና ዓሳ ልማት ገበያ ተኮር እንዲሆን በማድረግ፣ ውጤታማ የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር የግብርና ግብይትን በማዘመን እና ውጤታማነትን በማሻሻል፣ የግሉ ዘርፍ በገበያ ተኮር የግብርና ልማት በሰፊው እንዲሳተፍ በማድረግ እና የግብርና ዘርፍ እምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ የግብርና እና ሌሎች መሠረተ-ልማት ዝርጋታ እና አቅርቦትን በማሻሻል የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን እንዲያድግ ይደረጋል።

**ያደገ የገጠር ነዋሪዎች ገቢ እና የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር፦** በገጠር የስራ ፈጠራ እና የንግድ ስራዎች እንዲጎለብቱ በማድረግ፣ በገጠር ከግብርና ውጭ ያሉ ተያያዥነት ያላቸውን እና ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በማስፋት እና ለግብርናና ገጠር ልማት የፋይናንስ አቅርቦት እና ተደራሽነትን በማሻሻል የገጠር ነዋሪዎች ገቢ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲያድግ እና በገጠር የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

**ያደገ አካታችና ዘላቂ የግብርናና ገጠር ልማት፦** ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ የግብርና ልማት በማረጋገጥ፣ የሴቶች እና ወጣቶች ተሳትፎን በግብርናና ገጠር ልማት ውስጥ በማስፋት እና ዘላቂ የቆላማ አካባቢ ግብርና ሥርዓት እንዲጎለብት በማድረግ ቆላማ አካቢዎች ያላቸውን እምቅ የግብርና አቅም ስራ ላይ በማዋል እና በቆላማ አካባቢዎች ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ የግብርናና ገጠር ልማት አካታችና ዘላቂ እንዲሆን ይደረጋል።

**ሀገራዊ የምግብ እና ስነ-ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፦** የምግብ ዋስትና እና አደጋን የመቋቋም አቅምን በማጠናከር፣ የምግብና ስነ-ምግብ ዋስትና ሥርዓት በመገንባት

የግብርና ልማት የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና የሚመረት ምርት የዜጎችን አካላዊ እና አእምሯዊ እድገትና ጤናማነት የሚያረጋግጥ ሥርዓተ-ምግብ እንዲኖር ይደረጋል።

## 6 . ፖሊሲ የማውጣት ስልጣንና የፖሊሲው ወሰን

ይህ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ በግብርና ሚኒስቴር አመንጪነት ተዘጋጅቶና በሚኒስትሮች ም/ቤት ጸድቆ ተግባራዊ ይሆናል። ይህ ፖሊሲ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በገጠርና ከተማ ለሚከናወኑ የግብርና ምርት እና ግብይት ልማት፣ የደንና ተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ ጥበቃና ዘላቂ አጠቃቀም እንዲሁም የገጠር ልማት ማስተባበርን ይይዛል።

## 7 . የፖሊሲው የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር የፖሊሲው ፈፃሚ ተቋማት፣ የማስፈጸሚያ የህግ ማዕቀፎችና አሰራር ሥርዓት፣ የልማት ፕሮግራሞች እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 7.1 ፖሊሲውን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት

ይህንን ፖሊሲ ለማስፈጸም የበርካታ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ሚናና ኃላፊነት የሚጠይቅ ሲሆን የግብርና ሚኒስቴር እና የክልል ግብርና ተቋም በዋናነት ይተገብራል፣ ያስተባብራል፣ በተጨማሪም ሌሎች ፈፃሚ ተቋማት የየራሳቸው ጉልህ ድርሻ ያላቸው ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ➔ የብሔራዊ ባንክ፦ የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት ያመቻቻል፣ ለብድር ማስያዣነት አሰራር ይዘረጋል፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋት የሚያስችል አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች አሰራር ይዘረጋል፣
- ➔ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፦ የተቀናጀ መሬት አጠቃቀም ፖሊሲና እቅድ ያዘጋጃል፤ ምሉዕ እና ወቅታዊ ሀገራዊ የግብርና መረጃ ያጠናቅራል፣
- ➔ የትምህርት ሚኒስቴር፦ የከፍተኛ ትምህርት፣ ስልጠናና ተቋማት እና ኢንዱስትሪ (የግብርና ዘርፍ ተቋማት) ትስስርን ያስተባብራሉ፣ በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርትና ስልጠና በግብርና ዘርፍ የሰው ኃይልና ክህሎት ፍላጎት መሠረት እንዲመራ ያመቻቻሉ፤
- ➔ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፦ የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ፍላጎት ቀድሞ በመለየት በውል ግብርና አሰራር እንዲመረት ያመቻቻል። የእንስሳት መድሃኒትና ክትባት ማምረትና አቅርቦት ያመቻቻል፣ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት በኢንዱስትሪ የተቀነባበረ መኖ ማምረትና

አቅርቦት ያመቻቻል፣ የምርት ማቀነባበሪያ (አግሮ ኢንዱስትሪ) ዝርጋታን የማሳደግ ሥራ ይሰራል። በተጨማሪም ከማእድን ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የአፈር ማዳበሪያ በሀገር ውስጥ ማምረት፣ የግብርና ኖራ ማምረትና አቅርቦት እንዲሁም የፈሳሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረትና አቅርቦት፣ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማምረትና አቅርቦት ያስተባብራል፣ የሀገር ውስጥ መሳሪያዎች መገጣጠም ያመቻቻል፣

➔ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፦ የመሳሪያዎችን ደረጃ ያረጋግጣል (በደረጃዎች መዳቢ)፣ የግብርና ምርቶች የገበያ ትስስር ይፈጥራል፣ የወጪ ግብርና ምርቶች መዳረሻዎችን በማስፋፋት ለሀገር ውስጥ የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ ይሰራል፣ ጥራት ያለው ምርት እንዲመረት ባለሃብቱን የማበረታታት ተግባራትን ያከናውናል፤ የገበያ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ማሳደግን ያስተባብራል፣ ለዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል። ለሀገር ውስጥና ለውጪ ንግድ ገበያዎች በፍላጎት መሠረት በቅድሚያ እንዲመረት የሚያስችል በግብርና ምርት ውል አሰራር እንዲመረት ያመቻቻል፣

➔ የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር፦ ለግብርና አማራጭ የኃይል አቅርቦት ማስፋፋት እና የትላልቅ ውሃ ተፋሰሶች ልማትን ያስተባብራል፣

➔ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር፦ የገፀ-ምድር እና ከርሰ-ምድር ውሃን መሠረት ያደረገ የመስኖ አውታሮችን በመገንባት የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣ የመስኖ አውታር የርክክብ፣ ኦፕሬሽንና አስተዳደር ሥርዓትን ማሻሻል እና የመስኖ አውታር የፋይናንስ አሰራር (የውሃ ክፍያ፣ ወጪ መጋራት ወዘተ) እና የቆላማ አካባቢ የመስኖ መሠረተ-ልማት ይዘረጋል፣

➔ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፡- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ቴሌኮም አገልግሎት አቅርቦት የማሳደግ ሥራ ይሰራል፣ እንዲሁም በስራቸው የሚገኙ የምርምር ማእከላት ከግብርና ዘርፍ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ያደርጋል፣ የግብርናው ዘርፍ አዋጭ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም የቴክኖሎጂ ማስፋፋት ስራዎችን ይሰራል፣

➔ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር፦ የቀዝቃዛ ማጓጓዣና ማከማቻ እና ለግብርና ምርቶች ምቹ የሆነ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ማሳደግ እንዲሁም የተመረቱ ግብዓቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣

➔ ስራና ክህሎት ሚኒስቴር፦ ኢንተርፕረነርሽፕ ማጎልበቻ ስልጠና ይሰጣል፣ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣

➔ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን፦ የአደጋ ስጋትና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስራዎችን እና በአደጋ እና ግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች የእለት ደራሽ እርዳታዎች ማቅረብ፣ የመጠባበቂያ ክምችት እንዲኖር እና ልማቱንና ግብይቱን በሚያሳልጥ መልኩ ይሰራል፣

➔ የጤና ሚኒስቴር፦ የስነ-ምግብ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ጤናማ ምግብን መሠረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያ ማስተዋወቅና የስነ-ምግብ ትምህርት ማካሄድ ስራዎችን ያከናውናል።

## 7.2 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈጻጸም የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ሥርዓት

ይህን ፖሊሲ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ አዋጆች፣ ደንቦች እና የአሰራር ሥርዓቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

➔ በአዲስ መልክ የሚወጡ አዋጆች፦ የመሬት አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የተቀናጀ መሬት አጠቃቀም ፖሊሲ እና እቅድ አዋጅ፣ ባለብዙ ተዋንያን ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ አዋጅ፣ የእፅዋት ዘር አዋጅ፣ የእንስሳት ጤናና ደህንነት አዋጅ፣ ማዳበሪያና የአፈር ጤንነት ማሻሻያ ግብዓት ለማምረት ልማትና ቁጥጥርን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ፣ የመስኖ አውታር የርክክብ፣ ኦፕሬሽንና አስተዳደር አዋጅ፣ የመስኖ አውታር የፋይናንስ አሰራር (የውሃ ክፍያ፣ ወጪ መጋራት ወዘተ) አዋጅ፣ የእንስሳትና ዓሳ ርቢ አዋጅ፣ የዶሮና የዶሮ ውጤቶች ልማትና ግብይት አዋጅ፣ የንብ ውጤቶችና የኅብረ ንብ ግብይት አዋጅ፣ የዓሳ ሃብት ልማት፣ አጠቃቀምና ግብይት አዋጅ፣ የወተትና ወተት ውጤቶች ልማትና ግብይት አዋጅ፣ የግብርና ምርትን አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣ የአትክትልትና ፍራፍሬ ልማትና ግብይት አዋጅ፣ የእህል ሰብሎች ልማትና ግብይት አዋጅ፣ የስጋ እና የስጋ ውጤቶች ልማትና ግብይት አዋጅ፣ የተሻለ አቅም በመፈጠር ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን ወደ መካከለኛ ግብርና አልሚነት ለማሸጋገር የሚያስችል አዋጅ፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ መልቀቅ እና መመዝገብ ሁሉንም ተዋንያን እና ቴክኖሎጂዎች ባካተተ መልኩ የሚያስተናግድ የህግ ማዕቀፍ፣ የግብርና ንግድ ስራዎች አዋጅ፣ የግብርና ፋይናንስ (ብድርና አማራጭ ምንጭ) አዋጅ፣ የግብርና ኢንሹራንስ አዋጅ፣ ሰፋፊ የማሕበረሰብ ግጦሽ ቦታዎችን ጠብቆ ማቆየት የሚያስችል አዋጅ እና ሌሎችም የልማቱን እድገት ተከትለው ለሚመጡ አዳዲስ ሃሳቦችንና አሰራሮችን ለማስፈጸም የሚያስችሉ አዋጆች ታሳቢ ይሆናሉ።

➔ የሚሻሻሉ ወይም የሚሻሩ አዋጆች፦ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፣ የጀነቲክ ሃብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር 482/1998፣ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ፣ የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002፣ የእፅዋት ኳራንቲን አዋጅ፣ የዓሣ ሃብት ልማት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 315/1995 እና በጥናት ሲደገፍ ሌሎች በሥራ ላይ ያሉ አዋጆችን ይጨምራል።

→ በአዲስ መልክ የሚወጡ ደንቦች፦ የመሬት አስተዳደር ማቋቋም ደንብ፣ የተቀናጀ መሬት አጠቃቀም እቅድ ደንብ፣ የደን ልማት፣ አጠባበቅና አጠቃቀም ደንብ፣ የአነስተኛ የእርሻ መሬት ይዞታን ማሰባሰብና ማዋሃድ (Land Consolidation) ደንብ፣ የመንግስት የእንስሳትና የዓሳ ዝርያ ማሻሻያና ማባዣ ማዕከላት በከፊል ለትርፍ ወደሚሰሩ ተቋማትነት የሚቀየሩበት ደንብ፣ የህብረት ስራ ማህበራት ደንብ፣ የገጠር ልማትን የሚያስተባበር ተቋም ማቋቋሚያ ደንብ፣ የመንግስት ምርምር ሥርዓት ማሻሻያ (ምርምር በከፊል ለትርፍ የሚሰራበት አሰራርን ጨምሮ) ደንብ እና አዳዲስ በሚወጡ አዋጆች ላይ ደንብ እንዲወጣላቸው በሚወሰኑ አዋጆች መነሻነት የሚወጡ ደንቦችን ያካትታል።

## 7.3 ፖሊሲውን ለማስፈጸም የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞች

ዘላቂ ምርትና ምርታማነት እድገት ለማረጋገጥ የተለዩ የልማት ፕሮግራሞች፦ የግብርና ልማት ዋነኛ ምሰሶ የሆነውን መሬት እና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምን ለማጎልበት የመሬት እና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን የገጠር መሬት አስተዳርርና አጠቃቀም የሚያጎለብቱ፣ የደን ሃብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚያሳድጉ፣ የተፋሰስ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም እና የአፈር ለምነትና ጤንነትን የሚያሻሽሉ እና የብዝሃ-ህይወት ጥበቃና አጠቃቀም የሚያሳድጉ ኢንቨስትመንቶች የሚከናወኑ ይሆናል። ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ የምርምርና ስርጸት ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በዚህ ፕሮግራም በዋናነት የግብርና ምርምር ቴክኖሎጂ አቅርቦት የማሳደግ እና የግብርና የኤክስቴንሽና ምክር አገልግሎት የሚያሻሽሉ ቁልፍ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል። የምርትና ምርታማነት ማሻሻል በዋናነት በግብዓት በቂ እና ተደራሽ አቅርቦት የሚወሰን በመሆኑ የግብዓትና አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በዚህ ፕሮግራም የእፅዋት ዘር፣ የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ግብዓት፣ የእፅዋት ጥበቃ ግብዓት እና አገልግሎት፣ የእንስሳትና ዓሳ ዝርያና ዘር እና የርባታ ግብዓት አቅርቦት፣ የእንስሳት መኖ ልማት፣ ዝግጅትና አቅርቦት፣ የእንስሳትና ዓሳ ጤና ጥበቃ ግብዓትና አገልግሎት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀም የሚያበረታቱ ቀልፍ ኢንቨስትመንቶች የሚከናወኑ ይሆናል። በግብርና ልማት የውሃ አጠቃቀምን ማሻሻል ወሳኝ ከመሆኑ አንፃር የግብርና ውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን የግብርና ውሃ አቅርቦትን፣ የአነስተኛ መስኖ መሠረተ-ልማትን በማስፋፋትና ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ፣ የግብርና ውሃ አቅርቦትን የሰፋፊ መስኖ መሠረተ-ልማትን በማስፋፋት እና የሰፋፊ መስኖ መሠረተ-ልማት አስተዳደር ሥርዓት ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል። ከግብዓት፣ ቴክኖሎጂ አቅርቦት እና እምቅ የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም እና ለመንከባከብ ከሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶች በተጨማሪ የግብርና ዘርፍን አቅም በቀጣይነት ማጎልበት ወሳኝ በመሆኑ የዘርፉን የማስፈፀም አቅም

ግንባታ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በዚህ ፕሮግራም ስር የግብርና ዘርፉን የሰው ኃይል ልማት፣ የዲጂታል ግብርና እና ኮሙኒኬሽን አሰራር እና የቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት እና ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር የሚያጠናክሩ ኢንቨስትመንቶች የሚከናወኑ ይሆናል።

**የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ለማጎልበት የተለዩ የልማት ፕሮግራሞች፦** አነስተኛ ይዞታ አርሶ አደርና አርብቶ አደር የሰብል፣ እንስሳት እና ዓሳ ምርት ገበያ ተኮር የልማት ፕሮግራሞች፣ የህብረት ስራ ማህበራት አሰራር ማሻሻያ ፕሮግራም፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና ውጤታማነት ፕሮግራም እና የግብርናና ገጠር ልማት ያልተማከለ የመሠረተ-ልማት ዝርጋታና አቅርቦት ልማት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋሉ። በተለይም ከውጭ የሚገቡ ሰብሎችን (ስንዴ፣ ሩዝ እና የምግብ ዘይት) በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፤ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደርና አርብቶ አደር የእህል ሰብሎች፣ ሆርቲካልቸር ልማት፣ ቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም ልማት፣ የጥጥ ልማት፣ የወተት ልማት፣ የዶሮ ልማት፣ የማር ልማት፣ የቀይ ስጋ ልማት እና የዓሳ ልማት ለማሻሻል የሚከናወኑ የጥሬ እቃ አቅርቦት፣ የግብይት ሰንሰለት እና ገበያ ትስስር እና ሌሎች መሠረተ-ልማት ለማሟላት ይህ ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። የህብረት ስራ ማህበራት አሰራር ማሻሻያ ፕሮግራም የኅብረት ሥራ ማህበራትን በነፃ ገበያ ሥርዓት ውስጥ ይበልጥ ውጤታማነት እንዲያድግ የማዘመን እና አቅምን የማሳደግ እንዲሁም የሚያስፈልጓቸው መሠረተ-ልማቶች እና ግብዓቶች እንዲሟሉ ለማድረግ ይህ ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና ውጤታማነት ፕሮግራም የተሻለ አቅም በመፍጠር ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን ወደ ኮሜርሻል የግብርና አልሚነት እንዲሸጋገሩ ለመደገፍ የሚሰሩ ተግባራትን ለማገዝ እንዲሁም የግል ሴክተሩ ሰፋፊ የግብርና ልማት ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚከናወን ይሆናል። የግብርና ልማት ያልተማከለ የመሠረተ-ልማት ዝርጋታና አቅርቦት ልማት ፕሮግራም ግብርናን ያማከለ እንዲሁም የምርት መጠን፣ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ መሠረተ-ልማት ለማከናወን ተግባራዊ ይደረጋል።

**የገጠር ነዋሪዎች ገቢ ለማሳደግ እና የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ የተለዩ የልማት ፕሮግራሞች፦** የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ስራዎች ማሳደግ (Agrienterpreurship)፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ እና የፋይንናስ አቅርቦትና ተደራሽነት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ስራዎች ማሳደግ (Agrienterpreurship) ፕሮግራም የግብርና ግብዓትና አገልግሎት አቅርቦት ለማሳደግ እና የግብርና የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ ስራዎች ለማሻሻል የሚከናወኑ ስራዎችን የሚደግፍ ይሆናል። በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ፕሮግራም የተቀናጀ የገጠር ልማት ስራዎች ለማሳደግ እና የገጠር ነዋሪዎች ኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎትን ለማሳደግ የሚከናወኑ ስራዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የግብርና ልማት የፋይንናስ አቅርቦትና ተደራሽነት

ፕሮግራሞች ለዘርፉ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦትን ለማሻሻል እና የግብርና ኢንሹራንስ እንዲጎለብት የሚከናወኑ ስራዎችን ለማገዝ ተግባራዊ ይደረጋል።

**የግብርናና ገጠር ልማት አካታችና ዘላቂ ለማድረግ የተለዩ የልማት ፕሮግራሞች፦** ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተስተጋበረ የዘላቂ ግብርና፣ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እና ዘላቂ የቆላማ አካባቢ ግብርና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ። ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተስተጋበረ የዘላቂ ግብርና ፕሮግራም ከግብርና ዘርፍ ሚመነጨውን የሙቀት አማቂ ጋዞች የሚቀንስ ስራዎችን ለማስፋፋት እና የአካባቢ ሚዛንን የጠበቀ ዘላቂ ግብርና አሰራሮችን ለማሳደግ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ፕሮግራም የሴቶችን ጉልበት የሚቆጥብ የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ለማስፋፋት እና የሴት አርሶና አርብቶ አደሮች ተሳትፎና የኢኮኖሚ አቅም የሚያሳድጉ የግብርና ንግድ ስራዎች (Agribusiness) ለማስፋፋት ተግባራዊ ይሆናል። ዘላቂ የቆላማ አካባቢ ግብርና ፕሮግራም የቆላማ አካባቢ ግብርና ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ የአካባቢውን ሥርዓተ-ምህዳርንና የአኗኗር ዘይቤን ባገናዘበ መልኩ ለማስፋፋት እና ውሃን ማእከል ያደረገ የግብርና ልማት ለማሳደግ ይህ ፕሮግራም ተፈፃሚ ይሆናል።

**የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የተለዩ የልማት ፕሮግራሞች፦** የምግብ ዋስትና እና አደጋን የመቋቋም አቅም ማጠናከር እና የምግብና ሥነ- ምግብ ዋስትና ሥርዓት ግንባታ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የምግብ ዋስትና እና አደጋን የመቋቋም አቅም ማጠናከር ፕሮግራም የልማታዊ ስፍቲኔት የምግብ ዋስትና እና በድርቅና ግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች የምግብ ሥርዓት እና አማራጭ የገቢ ምንጭ ለማጠናከር የሚከናወኑ ስራዎችን የሚያግዝ ይሆናል። የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና ሥርዓት ግንባታ ፕሮግራም ከአደጋ መከላከል ባለፈ የሥርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና ለማስፋፋት እና የሥርዓተ ምግብ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚከናወኑ ቁልፍ ስራዎችን ለመደገፍ ተግባራዊ ይደረጋል።

## 7.4 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈጻጸም የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የግብርና ዘርፍን ፖሊሲ ለመከታተል እና ውጤታማነቱን ለመለካት በየደረጃው ያሉ ሁሉንም አስፈፃሚ ተቋማት እና ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ የሚመራ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል። ይህም ፖሊሲው የሚጠበቅበትን ውጤት እንዲያስገኝ ብሎም ፖሊሲውን የማያሰሩ ጉዳዮችን በመለየት ፖሊሲውን እስከማሻሻል የሚያስደርስ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችላል።

ፖሊሲው የታለመለትን ዓላማ እያሳካ መሆኑን በተገቢው ሁኔታ ለመለካት የሚያስችሉ መለኪያዎችን በማስቀመጥ ከግብዓት እስከ የፕሮግራም ውጤቶች እንዲሁም የፕሮግራሙ ውጤቶች ፋይዳን በሚያመላክት መልኩ የተቀመጠውን የፕሮግራሞች አተገባበር የእሳቤ ማዕቀፍ መሠረት በማድረግ የፖሊሲውን የስኬት መጠን በየጊዜው በመከታተል በተቀመጡ የፖሊሲው ቁልፍ የስኬት አመላካቾች

ላይ የሚስተዋሉ ለውጦችን በመለካት ሳይንሳዊ የግምገማ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚተነተን እና የሚገመገም ይሆናል።

የፖሊሲ ቁልፍ የውጤት አመላካቾች ልኬት በምን ያህል ድግግሞሽ፣ ጊዜ፣ የት እና እንዴት ክትትል እንደሚደረግባቸው፤ በምን ያህል ጊዜና ምን ዓይነት የግምገማ ዘዴን በመከተል የግምገማ ስራው እንደሚከናወን፣ በግምገማ ሂደቱ የሚሳተፉ አካላት እንዴት እንደሚለዩ፣ የግምገማ ስራው የሚያስፈልገው ወጪ በማን እና እንዴት እንደሚሸፈን እንዲሁም የግምገማ ሪፖርት ዝግጅት እና ስርጭት የሚያመላክት አሳታፊ የክትትልና ግምገማ ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የዲጂታል የክትትልና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትን ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችል የግብርና መረጃ ፍሰት ሥርዓት ይዘረጋል።

ክትትልና ግምገማ የፖሊሲውን መጽደቅ ተከትሎ የሚፈጸም ዋነኛ ጉዳይ ነው። ይህም ፖሊሲው የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች እና ንዑስ ፕሮግራሞች ትግበራ አፈፃፀም ለመከታተል የሚያግዝ ተግባር ሲሆን ዓላማውም የሚተገበሩ ፕሮግራሞች አፈፃፀም በእቅዱ መሠረት እየተካሄደ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የግብዓት አጠቃቀም፣ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን እና እየተመዘገቡ ያሉ ውጤቶችን መረጃ በማደራጀት የፕሮግራሞቹን የጊዜ፣ ወጪ እና አፈጻጸም ለሚመለከታቸው አካላት ይፋ በማድረግ ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን እንዲሁም የፕሮግራም ማስተካከያዎችን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት በቂ ምክንያት ለማቅረብ ማስቻል ነው።

የፖሊሰው ትግበራ ግምገማ በመተግበር ላይ ባሉ እንዲሁም በተጠናቀቁ ፕሮግራሞች ላይ ስልታዊ በሆነ መልኩ ከንድፍ፣ ከአተገባበር እና ካስገኙት ውጤት አንፃር በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ተጨባጭ ግምገማ ይደረጋል። ግምገማዎቹ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የፕሮግራሙን አግባብነት፣ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና፣ የፕሮግራሙ ውጤቶች ተፅእኖ እና ዘላቂነትን በሚገባ ያሳያሉ። በዚህም በፖሊሲ ትግበራው ትክክለኛውን ነገር እየሰራን መሆኑን ማለትም የተገኙ ውጤቶች በፕሮግራሙ መተግበር የመጡ መሆናቸውን እና ፕሮግራሙ ባይተገበር ምን ይፈጠር ነበር የሚለውን ለማወቅ እንዲሁም በፖሊሲ ትግበራው ትክክለኛውን ነገር በትክክል እየሰራን ስለመሆናችን ማለትም የፕሮግራም ትግበራው ሂደት ፕሮግራሙን በብቃት እና በቅልጥፍና ለመተግበር እንዲሁም ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት ያስችላል ወይ? የሚሉ ጉዳዮችን ለመመለስ የሚያስችል ነው።

ግምገማው ስለፕሮግራሙ ማወቅ ወይም መማር በምንፈልገው ጉዳይ ላይ በመመስረት ሁለት ዓይነት ዋና ዋና ግምገማዎች የሚደረጉ ሲሆን የመጀመሪያው የሂደት ግምገማ ነው። ይህም በሂደት ላይ ያተኮሩ እና በፕሮግራሙ ትግበራ ወቅት ውሳኔ አሰጣጥን ለማገዝ ስልታዊ የመረጃ መሰብሰብን መሠረት በማድረግ የሚከናወን የግምገማ

ዓይነት ሲሆን ይህም የመካከለኛ ዘመን የትግበራ ግምገማ ወይም የፕሮግራሙ ትግበራ በሂደት ላይ እያለ በተለያዩ ጊዜያት ሊከናወን ይችላል። ዓላማውም የፕሮግራሙ አተገባበር ሂደትን ለመገምገም፣ የፕሮግራሙን ውጤቶች እና ውጤቱን ተከትለው ስለሚመጡ ለውጦች ለመተንበይ እንዲሁም በፕሮግራሙ ንድፍ ውስጥ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ለማመላከት ነው።

ሁለተኛው ዓይነት የትግበራ ግምገማ የማጠቃለያ ግምገማ ሲሆን ይህ የውጤት ወይም የተፅዕኖ ግምገማ ከመሆኑ አኳያ የማጠቃለያ ግምገማ የሚከናወነው ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው። ዓላማውም ከትግበራው የተገኙ ስኬቶችን፣ ተፅእኖዎችን እና የቀሰምናቸውን ትምህርቶች ለማጠቃለል ሲሆን ይህም ፕሮግራሙ ከተቀመጡት ግቦች አንጻር ምን እንዳከናወነ ያሳያል። ሁለት ዓይነት የማጠቃለያ ግምገማዎች የሚደረጉ ሲሆን፤ የመጨረሻ ግምገማ በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ የሚደረግ የፕሮግራሙን አፈፃፀም እና ተፅእኖ አጠቃላይ ግምገማ ለማቅረብ፣ ፕሮግራሙ ምን ያህል አላማውን ለማሳካት እና ዘላቂነቱን ለመገምገም ሲሆን የድህረ-ፕሮግራም ግምገማ ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ ከሁለት እስከ አምስት ዓመታት ባለው ጊዜ በማከናወን የፕሮግራሙን የመጨረሻ ፋይዳና ተፅእኖ በመገምገም የተገኙ ልምዶችን እና ትምህርቶችን በመቀመር ለቀጣይ ፖሊሲ ግብዓት እንዲሆኑ ማስቻል ያስፈልጋል።

በመሆኑም የፖሊሲውን ውጤታማነት ክትትልና ግምገማ ማድረግ የሚያስችል በዲጅታል ቴክኖሎጂ በክህሎት በዳበረ የሰው ኃይል የተሟላ እንዲሁም የአሰራ ሥርዓት የተዘረጋለት ጠንካራ የክትትልና ግምገማ የስራ ክፍል በየደረጃው ማደራጀት የሚያስፈልግ ሲሆን በክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ውስጥ ለሚሳተፉ ባለሙያችም ተገቢ የሆነ የማበረታቻና የማትጊያ ሥርዓት ማበጀት እንዲሁም ተከታታይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል። በተጨማሪም ወቅቱን ያገናዘበ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ በማከናወን ለዘርፉ አስተዋጽዖ በሚያደርግ አግባብ በየደረጃው የክትትልና ግምገማ አቅም የመገንባቱ ስራ የሚከናወን ይሆናል።

በተጨማሪም የክትትልና ግምገማ ውጤትን መሠረት በማድረግ በዘርፉ የግልጸኝነት አግባብን መዘርጋት አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ሲሆን በዚሁ ልክ የተጠያቂነት አሰራር የሚዘረጋበት አግባብም የሚኖር ይሆናል። ይህም ከአስተዳደራዊ እርምጃ ጀምሮ በህግ አግባብ እስከ መጠየቅ የሚደርስ ይሆናል። ይህም በየደረጃው ከከፍተኛ አመራሩ እስከ ታችኛው የመንግስት እርከን የሚገኘውን የዘርፉ ተዋንያኖችን ጨምር የሚያካትት ይሆናል።

## ፰. ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች

በግብርና ዘርፍና በገጠር የተለዩ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ውጤታማ በሆነ አግባብ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች ሚና ያላቸው ሲሆን በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም በግብርና ዘርፍ ውስጥ በስራ ላይ የሚገኙ ፖሊሲዎች በተለይም የእንስሳት ርቢ ፖሊሲ ከዚህ ፖሊሲ ጋር በተቀናጀ መልኩ ይተገበራል፡፡

### ፰.፩ የአምራች ዘርፍና የመሠረተ-ልማት ዘርፍ ፖሊሲዎች

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፖሊሲ በግብርና ተመርተው ለአምራች ዘርፉ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን በግብዓትነት በመጠቀም የግብርና ዘርፉን የመደገፍ እንዲሁም በአምራች ኢንዱስትሪ የሚመረቱ የግብርና ግብዓቶችን ጥራት ባለው መልኩ የማቅረብ፣ የግብርና ምርቶችን እሴት ሊጨምሩ የሚችሉ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ስራዎችን በመስራት የግብርና ምርቶች ተፈላጊነትን ማሳደግ፣ ለእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማደግ ወሳኝ የሆነውን የመኖ ማቀነባበሪያ ማስፋፋት እና በቂ የሆነ የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ እንዲኖር በማድረግ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ ለአሲዳማ አፈር ማከሚያ የሚሆን የኖራ አቅርቦት በጥራትና በስፋት በማቅረብ የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ መስራት፣ ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የአፈር ማዳበሪያ በሀገር ውስጥ ማምረት፣ የፀረ-አረም መድሀኒቶችን በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ናቸው፡፡ የንግድ ፖሊሲ በግብርናው ዘርፍ የሚመረቱ ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲመረቱ ከማድረግ አንስቶ የምርት መዳረሻዎችን ማስፋፋትና አማራጭ ገበያ እንዲኖር በማድረግ ከግብርና ምርቶች የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ፣ የግብርና ምርቶች ለማህበረሰቡ በአግባቡ የሚደርስበትና አላስፈላጊ የዋጋ ንረትን ለማስቀረት የንግድ ሰንሰለቱን የሚያሳጥር (አምራችና ሸማቹን ማገናኘት የሚያስችል) አሰራር በመዘርጋት በግብርና ምርት ላይ የሚስተዋልን የዋጋ ንረት መቀነስ፣ የግብርና ውጤቶች በተለይም የቁም እንስሳት ህገ-ወጥ ንግድን ወደ ህጋዊ አሰራር በማስገባት ዘርፉ ለሀገሪቱ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ ከንግድ ፖሊሲው የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ፖሊሲ የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የተፋሰስ ልማት እና የአፈር ጥበቃ ተግባራትን ተፋሰስን መሠረት በማድረግ ያከናውናል፣ የግብርና ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የኃይል አቅርቦት እንዲስፋፋ ያደርጋል በተለይም አማራጭ የኃይል አቅርቦት በገጠር እንዲስፋፋ ያደረርጋል፣ አርሶ አደሩ ውሃን በአግባቡ የሚጠቀምበትን የውሃ አጠቃቀም ዘለቄታዊ ባለው አግባብ እንዲመራ ያደርጋል፡፡ የመስኖ ፖሊሲ ግብርናን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ የሚያስችል የመስኖ ስራ በማስፋፋት የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል ስራዎች ይሰራል፡፡ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ፖሊሲ የግብርና ምርቶችን ወደ ገበያ ለማድረስ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ የመንገድ መሠረተ-ልማት ማስፋፋት፣

የግብርና ምርቶችን አሽጎ ወደ ውጭ በመላክ የሚደርሰውን ብክለት ይቀንሳል፣ ዘመናዊ የጭነት ትራንሰፖርት በመዘርጋት በግብርና ምርቶች ላይ የሚደርሰውን የትራንስፖርት ዋጋ ንረት የሚቀንስ ተግባርን ያከናውናል፣ ለግብርና ግብዓት የሚሆኑ የማዳበሪያና ሌሎች ግብዓቶችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ በማጓጓዝ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እና ለአርሶ አደሩ በወቅቱ እንዲሰራጩ ይደረጋል።

## 8.2 ማህበራዊና የሰው ሃብት ልማት ፖሊሲዎች

የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ በስልጠና ላይ የሚገኙ የግብርናና ተፈጥሮ ሃብት፣ የመስኖ ኢንጂነሪንግ እና የግብርና ቴክኒክና የስልጠና ትምህርት ክፍሎች የግብርናው ዘርፍ የሚፈልገውን ብቃትና ክህሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ማምረት፣ በግብርናው ዘርፍ ለሚሰማሩ አነስተኛና የግብርና ኢንተርፕራይዞች ግብርናውን ሊያዘምን የሚያስችል ስልጠና መስጠት የሚጠበቁ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

## 8.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ

በሀገር ደረጃ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ፣ የማላመድና ወደ ማምረት እንዲገቡ እና በሰፊው እንዲመረቱ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ልማት ምርምርና ጥናት በማካሄድ የግብርና ዘርፉን መደገፍ ከዚህ ፖሊሲ የሚጠበቅ ተግባር ነው። የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችና መሳሪያዎችን ደረጃዎችን ማስጠበቅና ማረጋገጥ።

## 9 . መሠረታዊ የቃላት ፍቺ

- "አርሶ አደር" ማለት ከግብርና ስራ ባገኘው ገቢ እራሱን እና ቤተሰቡን የሚያስተዳደር የኢኮኖሚ ተዋናይ ነው።
- "የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች" ማለት የመሬት ይዞታቸው ከአስር ሄክታር ያልበለጠና በጥምር እርሻ፣ በእርሻ ወይም በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩ የገጠር ማህበረሰብ አካል ናቸው።
- "አርብቶ አደር" ማለት የግጦሽ መሬት በመያዝና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ በዋነኝነት እንስሳት እርባታ ላይ ኑሮው የተመሰረተ የገጠር ህብረተሰብ አካል ነው።
- "ከፊል አርብቶ አደር" ማለት በዋነኝነት የግጦሽ መሬት በመያዝና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ላይ የተመሠረተ እንስሳት እርባታ እና በተወሰነ ደረጃ በእርሻ ላይ ኑሮው የተመሰረተ የገጠር ህብረተሰብ አካል ነው።
- "የመካከለኛና ሰፋፊ ግብርና" ማለት የንግድ ፈቃድ ኖሮት በካፒታልና እውቀት ላይ የተመሠረተ እና ከአስር ሄክታር በላይ የእርሻ መሬት ወይም ከተወሰነ የእንስሳት ቁጥር በላይ የሚከናወን የግብርና ልማት ነው።
- "ግብርና" ማለት በእንስሳትና ዓሳ፣ በሰብል (እህል፣ አትክልት፣ በፍራፍሬ፣ ቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም) እና በደን ምርት ማምረትን ፣ የምርት አሰባሰብን፣ ድህረ-ምርት አያያዝን፣ የእሴት ጭመራ፣ ግብይት እና አጠቃቀም ያለውን ሂደት እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀምን የሚያካትት ዘርፍ ነው።
- "ግብርናን ማሻገር" ማለት ለገበያ የሚያመርት፣ ከፍተኛ ቴክኖሎጂና ግብዓት የሚጠቀም፣ የላቀ የሰው ኃይል ምርታማነት፣ እሴት የሚጨምር ሆኖ የዘመነ፣ አሳታፊና ዘላቂ የግብርና ሽግግር የሚያመጣ ሂደት ነው።
- "የገጠር ነዋሪ" ማለት በገጠር በግብርና ስራ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን እና በሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ኑሮው የተመሠረተ ከከተማ ክልል ውጭ የሚኖር የማህበረሰብ ክፍል ነው።
- "የገጠር ልማት" ማለት የገጠር ነዋሪዎች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ለማሻሻል የሚተገበር ሥራ ሲሆን በዋናነት የግብርና ልማት፣ የምግብ ዋስትናና ድህነት ቅነሳ እንዲሁም በገጠር ከግብርና ውጪ የሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማት ማስፋፋትን ያካትታል።
- "የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር" ማለት የገጠር ነዋሪዎች ሁለንተናዊ የለውጥ ጉዞ የሚያመላክት ሆኖ በግብርና ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ ያለውን የኑሮ መሰረታቸውን በማሰባጠር በገጠር ወደ ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እና የቢዝነስ ዕሳቤዎች ተስፋፍተው በገጠርና በከተማ ጠንካራ የንግድና አገልግሎት ግንኙነት መፍጠር ነው።
- "የገጠር መሬት" ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጭ ወይም አግባብ ባለው ሕግ ከተማ ተብሎ ከሚሰየመው ውጭ ያለ ማንኛውም መሬት ነው።
- "መሬት ማሰባሰብና ማዋሃድ" (Land consolidation) ማለት አነስተኛ መሬት ባለይዞታዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የተበጣጠሱ መሬቶችን በማለዋወጥ እና ኩታ ገጠም በማድረግ እንዲሁም የጋራ ባለቤትነት በማስፈን በሂደትም ካፒታልና እውቀት

የያዙ ተዋንያኖች በጋራ የሚያሳትፍ የማምረት ዘይቤ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ፣ ግብይትና ማቀነባበር ተግባራትን ያካትታል።

- "ቴክኖሎጂ" ማለት በግብርናው ዘርፍ በሚደረጉ የምርምርና ፈጠራዎች ውጤት ሲሆን የእፅዋት እና እንስሳትና ዓሳ ዘርና ዝርያዎች፣ ስነ-ህይወታዊና የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች፣ አዳዲስ እና የተሻሻሉ የእርሻ መሳሪያዎች፣ ደቂቅ አካላት፣ መድሃኒታማና መአዛማ ኬሚካሎች፣ የሰብልና እንስሳት ጤና ጥበቃ የምርምር ውጤቶች፣ የእንስሳት መኖና ስነ-ምግብ እንዲሁም የአሠራርና የአመራረት ስልቶች ምክረ-ሃሳብን ያካትታል።
- "ግብዓት" ማለት ከምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎች ተባዝተው ለተጠቃሚዎች የሚደርሱ የሰብል፣ እንስሳትና ዓሳ እና ደን ምርታማነትን የሚያሳድጉ፣ የሰው ኃይል ምርትማነትን የሚጨምሩ፣ የአፈር ለምነትና ጤንነት የሚያሻሽሉ፣ የእፅዋት እና እንስሳት ጤናን የሚጠብቁና የሚከላከሉ፣ የመሬት ደህንነት ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስፈልጉትን እና የመሳሰሉትን ያካትታል።
- "አገልግሎት" ማለት ቴክኖሎጂና ግብዓትን (ተያያዥ ዕውቀትና ክህሎት ጨምሮ) ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ሲሆን የኤክስቴንሽንና ምክር፣ የሜካናይዜሽን፣ የእፅዋት ጥበቃ፣ የእንስሳት ጤናና ደህንነት እና የመሳሰሉትን ያካትታል።
- "የግብርና ውሃ" ማለት ከዝናብ ከገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር ምንጮች የሚገኝ ውሃ ሰብል ለማምረት፣ ለእንስሳትና ዓሳ እርባታ፣ ለተፈጥሮ ሃብትና ለደን ልማት የተለያዩ የውሃ አጠቃቀም ስልት በማቀናጀት የመስኖ ልማትን፣ የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝን ያካትታል።
- "ረቂቅ ግብርና" (Precision Agriculture) ማለት የማምረቻ ግብዓቶችን ብክነት በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀንስ የግብርና አሰራር ሆኖ ባደገ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የአመራረትና ምርት ላይ አዋኪ ስነ-ህይታዊም እና ኢ-ህይወታዊ ተግዳሮቶችን የሚቋቋም፣ ስማርት (Smart) ግብርና ሥርዓቶችን የተከተለ፣ የመረጃ ቅብብሎሽና ፍሰት ማቀላጠፊያዎች እና የጂዮግራፊካል ኢንፎርሜሽን ሲስተም (የጂ.አይ.ኤስ) ቴክኖሎጂ ግብርናን ያካትታል።
- "አካታች" ማለት ሁሉንም የግብርናና ገጠር ልማት የሚመለከታቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር፣ የከተማ ግብርና ተዋንያን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የግል አልሚዎች፣ የአካል ጉዳተኞችና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን መሠረት በማድረግ የምግብና ስነ-ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው።
- "የምግብ ሉዓላዊነት" ማለት ከምግብ ተመጽዋቾነት ለመላቀቅ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት የግብርና ምርትና ምርትማነትን በማሳደግ በምግብ እራስን መቻል።
- "ካፒታል" ማለት ወደ ግብርና ዘርፍ ከተለያዩ ተዋንያን የሚፈስ ገንዘብ እና የግብርና ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ አካላዊ ግብዓቶችን ያካተተ ነው።
- "የፆታ አገላለፅ" በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

Ethiopian ATI
Agricultural Transformation Institute
የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት